የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COMMISSION

በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የተዘጋጀ

# የፍርድ ቤቶች እና ፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች ለአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን የተደራሽነት ሁኔታ ሪፖርት



Phot o Credit: Getachew Asnakew, Media and Communications Department, EHRC

የካቲት 2016 ዓ.ም.

www.ehrc.org

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COMMISSION

# ማውጫ


**አንኳር ጉዳዮች ........ I**

**የክትትሉ ዋና ዋና ግኝቶች ........ II**

መልካም ጅማሮዎች ........ II

አሳሳቢ ጉዳዮች........ III

ምክረ ሐሳቦች ........ IV

**ክፍል አንድ ........ 1**

መግቢያ........ 1

የክትትሉ ዓላማ ........ 3

የክትትሉ ሥነ-ዘዴ........ 3

የክትትሉ ወሰን እና ጊዜ ........ 4

**ክፍል ሁለት ........ 5**

አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን የተመለከቱ ቁልፍ ፅንሰ ሐሳቦች........ 5

የፍትሕ ሥርዓት ተደራሽነት የሕግ ማዕቀፎች እና መርሖች ........ 6

ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች........ 6

አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ሕጎች ........ 7

ብሔራዊ ሕጎች........ 8

አግባብነት ያላቸው ዓለም አቀፍ መርሖች........ 9

**ክፍል ሦስት ........ 10**

የክትትሉ ግኝቶች........ 10

ተቋማዊ ተደራሽነት........ 10

ከባቢያዊ ተደራሽነት ........ 17

የመረጃና ተግባቦት ተደራሽነት........ 18

የአመለካከት መሰናክሎች ........ 20

**ክፍል አራት ........ 23**

ማጠቃለያ እና ምክረ ሐሳቦች ........ 23

ምክረ ሐሳቦች ........ 23

# አንኳር ጉዳዮች

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ/ኮሚሽኑ) በሕግ ከተሰጡት ሥልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነቶች መካከል የሰብአዊ መብቶች ክትትል ማድረግና ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገባቸውን ምክረ ሃሳቦች ማቅረብ አንዱ በመሆኑ በተለይ ለሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ታሳቢ ያደረጉ የክትትል ሥራዎችን ያከናውናል፡፡ በዚህ መሠረት ኮሚሽኑ የፍትሕ ተቋማት አገልግሎቶች ለአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ባላቸው ተደራሽነት ዙሪያ የሰብአዊ መብቶች ክትትል አካሂዷል፡፡

ለዚህ የክትትል ሥራ መነሻ የሆነው በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የተመረጡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ከባቢያዊ ተደራሽነት ዙሪያ ከግንቦት 23-24 ቀን 2014 ዓ.ም. ተደርጎ የነበረ የሰብአዊ መብቶች ክትትል ሲሆን፣ በክትትሉ የፍርድ ቤቶቹ ሕንጻዎችና ምድረ-ግቢዎች ያላቸው የከባቢያዊ ተደራሽነት ጉድለት የፍትሕ ሥርዓት ተደራሽነት መብትን ለማረጋገጥ ተግዳሮት መሆኑን ኮሚሽኑ ለመረዳት ችሏል፡፡ የክትትሉም ግኝቶች በዚህ ሪፖርት ተካቷል፡፡ ኮሚሽኑ የክትትል ሥራውን በማስፋት የፍርድ ቤቶችና የፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች ሁለንተናዊ ተደራሽነትን በተመለከተ በተመረጡ በአፋር፣ በአማራ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በኦሮሚያ፣ በሶማሊ እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች በሚገኙ የፍትሕ ተቋማት ከታኅሣሥ 17 እስከ 22 ቀን 2015 ዓ.ም. እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የፌዴራል ፍትሕ ተቋማት ላይ ከታኅሣሥ 24 እስከ ጥር 6 ቀን 2015 ዓ.ም. የሰብአዊ መብቶች ክትትል አከናውኗል፡፡

በዚህ የክትትል ሥራ ኮሚሽኑ አካል ጉዳተኛ ባለሞያዎችን ያካተተ ቡድን በማሰማራት ከአካል ጉዳተኛና አረጋውያን ተገልጋዮች፣ ከፍርድ ቤቶችና ፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች ኃላፊዎችና ሠራተኞች፣ ከአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ማኅበራት እንዲሁም የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ መሥሪያ ቤቶች ኃላፊና ሠራተኞች ጋር በተደረጉ ቃለ መጠይቆች፤ በአካል ምልከታ እና ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሰነዶች በማመሳከር መረጃዎችና ማስረጃዎችን ሰብስቧል፡፡ ኮሚሽኑ በክትትሉ በአጠቃላይ ከ177 ሰዎች (40 ሴቶች እና 137 ወንዶች) ጋር ቃለ መጠይቆችን ያደረገ ሲሆን፤ ከእነዚህም መካከል 39 አካል ጉዳተኞች (12 ሴቶችና 27 ወንዶች) እና ከ60 - 75 ዕድሜ እርከን የሚገኙ 20 አረጋውያን (6 ሴቶችና 14 ወንዶች) በቃለ መጠይቁ ላይ ተሳትፈዋል፡፡

በተጨማሪም ከሰብአዊ መብቶች ክትትሉ መልስ በተዘጋጀው ረቂቅ ሪፖርት የተለዩ ዋና ዋና አሳሳቢ ጉዳዮች እና የቀረቡ ምክረ ሐሳቦች ላይ ለመመካከር ክትትሉ የተደረገባቸው ፍርድ ቤቶችና ፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች፣ ከተለያዩ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች የተውጣጡ ተወካዮች፣ የመንግሥት ልዩ ልዩ ተቋማት ኃላፊዎች፣ የአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ማኅበራት ተወካዮች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በተገኙበት በሰኔ 7 እና 25 ቀን 2015 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ እንዲሁም በሰኔ 28 ቀን 2015 ዓ.ም. በጅማ ከተማ በአጠቃላይ ሦስት ተከታታይ የምክክር መድረኮችን በማዘጋጀት ውይይት ተካሂዷል፡፡

የሰብአዊ መብቶች ክትትሉ ያተኮረው ፍርድ ቤቶች እና ፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች ላይ ሲሆን፤ ክትትሉ በተደረገባቸው የፍትሕ ተቋማት ውስጥ ከተደራሽነት መብት አንጻር በአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ላይ የሚደርሱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችና ለአካል ጉዳተኞች የሚደረጉ

የተመጣጣኝ/ምክንያታዊ ማመቻቸት (Reasonable Accomodation) እርምጃዎች ያሉበትን ደረጃ ለይቷል፡፡ በዚህም መሠረት የክትትሉ ዋና ዋና ግኝቶች እና ምክረ ሐሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

# የክትትሉ ዋና ዋና ግኝቶች

## መልካም ጅማሮዎች

ክትትል በተካሄደባቸው ፍርድ ቤቶች እና የፍትሕ ተቋማት የተጀመሩ የተለያዩ መልካም ተሞክሮዎች ያሉ ሲሆን ከእነዚህም መካከል የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

- በአፋር ክልል አካል ጉዳተኞችን፣ አረጋውያንን እና ሌሎች ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ያማከለ ነጻ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት፣ በጠበቆች በነጻ መወከል እንዲሁም የንቃተ ሕግ የግንዛቤ ማስፋፊያ የአሠራር ሥርዓት በክልል ደረጃ መዘርጋቱና ለወደፊትም ወደ ወረዳዎች ለማስፋፋት ዕቅድ መያዙ፤
- በኦሮሚያ እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ተገልጋዮችን የሚያስተናግዱ ባለሙያዎችን በመመደብ የጽሑፍ አገልግሎት (የክስ፣ የመልስ፣ የይግባኝ እና የማመልከቻ ጽሑፍ ድጋፍ በማድረግ)ቅድሚያ በመስጠት እንዲሁም የፍትሕ ተቋማቱ የተቋማቸውን ከባቢያዊ ተደራሽነት ለማሻሻል በስትራቴጂክ ዕቅዳቸው ውስጥ በማካተት ሥራ መጀመራቸው፤
- በአማራ ክልል ፍትሕ ቢሮ የተቋቋመው የሰብአዊ መብቶች ዳይሬክቶሬት የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ሲፈጸም ፖሊስ ምርመራ እንዲያደርግ ትዕዛዝ የሚሰጥ እና በጋራ ምርመራውን የሚያካሂድ መሆኑ፤ ከሕፃናትና ከሴቶች ጥቃት ጋር በተያያዘ ክርክር ሲደረግ እና የምስክር ቃል ሲሰጥ በማኅበራዊ ባለሙያዎች አማካኝነት ለተበዳዮች ወይም ሕጻናትን ጨምሮ አገልግሎቱ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች የምክርና የሥነ ልቦና ማረጋጋት ሥራ የሚከናወን መሆኑ፤
- የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፍትሕ ቢሮ የሚጠቀምበት የሰነድ ማረጋገጥና ምዝገባ የአሠራር ማኑዋል ወደ ተቋሙ ለአገልግሎት የሚመጡ ሰዎች የሚስተናገዱበትን ሥርዓት በዝርዝር ያመላከተ ሲሆን፤ በዚህ መሠረት የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊዎች፣ ባለሙያዎች እና አረጋጋጮች መስማት የተሳናቸውና በምልክት ቋንቋ የሚግባቡ ሰዎች ከማኅበራቸው አስተርጓሚ በደብዳቤ የተመደበላቸው መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚገባቸው በግልጽ ማስቀመጡ፤
- በሶማሊ ክልል ፍርድ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 206/2013 አንቀጽ 24 መሠረት አካል ጉዳተኛ ሕጻናትን ጨምሮ ከሕፃናት ጋር የተገናኘ የፍርድ ሂደት በዝግ ችሎት የሚታይ መሆኑ እና ዳኞችም ሆኑ ዐቃቤያነ ሕግ የችሎት ክብር ልብስ/ካባ ሳይለብሱ የችሎት ሂደቱ ለሕፃናት በማይከብድ ሁኔታ ወይም በሕጻናት ሥነ ልቦና ላይ አሉታዊ ተጽእኖ በማያሳድር መልኩ የሚካሄድ መሆኑ፤
- በአዲስ አበባ ከተማ ክትትል የተካሄደባቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ቅድሚያ እንዲሰጣቸው የሚያስችል የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያ ያለ መሆኑ፣ ይኸውም በፍርድ ቤት ዕቅድ ውስጥ እንዲካተት የሚደረግ እና አተገባበሩን

ለማወቅም በየክፍሎቹ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑ፤ በዚህ መመሪያ መሠረት ለአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ቅድሚያ እንዲስተናገዱ የሚያደርግ “ቅድሚያ” የሚል ባጅ እና ፎርም መኖሩ፣ በተመሳሳይ አሠራር የፍትሕ ቢሮ ጽሕፈት ቤቶች መሰል መመሪያ ባይኖራቸውም አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ቅድሚያ አገልግሎት እንዲያገኙ እንደሚደረግ በሪፖርቱ ከተካተቱ መልካም ጅማሮዎች መካከል ናቸው።

## አሳሳቢ ጉዳዮች

### ተቋማዊ ተደራሽነት

ኢሰመኮ በክትትል ሥራው በሸፈናቸው ፍርድ ቤቶች እና የፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን ከማካተት አንጻር የተለየ የበጀት ዕቅድ፣ ፖሊሲዎች ወይም መመሪያዎች አለመኖራቸውን እንዲሁም የአካል ጉዳተኞችና አረጋውያንን ፍላጎቶች መሠረት ያደረገ የአሠራር ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑን፣ ለሴት አካል ጉዳተኞች ተደራራቢ የመብት ጥሰት ተጋላጭነት ያገናዘበ የአሠራር ሥርዓት አለመኖሩን ተረድቷል።

ለአካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እንዲሁም ሌሎች ለመብት ጥሰት ተጋላጭ ለሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ነጻ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት የሚሠጥ፤ ጠበቆች በነጻ ጥብቅና እንዲቆሙላቸው የሚያደርግ እና ንቃተ ሕግን በተመለከተ ግንዛቤ የሚፈጠርበት የአሠራር ሥርዓት ቢኖርም ክትትሉ በተደረገባቸው ቦታዎች በወረዳ ደረጃ ወደሚገኙ ፍርድ ቤቶች እና ፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች አሠራሩ ባለመውረዱ የፍትሕ ተደራሽነት ክፍተቶች እንዳሉ ኮሚሽኑ ተመልክቷል።

በተጨማሪም በችሎቶች የክርክር ወይም የምስክር ቃል የማሰማት ሂደቶች ላይ ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት ተጎጂ አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን፣ ለአካል ጉዳተኛ ሕፃናትና ሴቶች፣ ለአእምሮ ሕሙማን ወይም የአእምሮ እድገት ውስንነት ላለባቸው ባለጉዳዮች የጉዳት ዐይነታቸውን እንዲሁም ተደራራቢ የመብት ጥሰት ተጋላጭነታቸውን ታሳቢ ያደረገ ምቹ የሆነ የአሠራር ሥርዓት አለመኖሩን ኮሚሽኑ ተገንዝቧል።

### ከባቢያዊ ተደራሽነት

ክትትሉ ከተደረገባቸው 41 የፍትሕ ተቋማት ውስጥ አራቱ (የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አዲስ ከተማ ምድብ ችሎት፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የአፋር ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የጅማ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት) ከአንድ ወለል በላይ ባላቸው ሕንጻዎች ላይ የሚገኙ ሲሆን ወደ ውስጥ ለመግባት ራምፕ (የተሽከርካሪ ወንበር መወጣጫ) ያልተገነባላቸው፣ አሳንሰር ያልተገጠመላቸው ናቸው። ባለ አንድ ወለል ሕንጻዎች ውስጥ የሚገኙ የፍትሕ ተቋማትም ራምፕ ያልተገነባላቸው፣ ባለ ደረጃ መግቢያ በሮች ያላቸው በመሆኑ የከባቢያዊ ተደራሽነት ክፍተቶች ያለባቸው መሆኑን ኮሚሽኑ ተገንዝቧል። ለአብነት፦ የችሎት አዳራሾች፣ መግቢያ በሮች፣ መጸዳጃ ቤቶች ለአካል ጉዳተኞች በተለይም ለተሽከርካሪ ወንበር (wheelchair) ተጠቃሚዎች ተደራሽ አለመሆናቸውን ኮሚሽኑ ተመልክቷል።

### የመረጃና ተግባቦት ተደራሽነት

ክትትል በተደረገባቸው ሁሉም ፍርድ ቤቶችና ፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች መስማት ለተሳናቸው ባለጉዳዮች የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ ያልተመደበ በመሆኑ፤ መስማት የተሳናቸው ተገልጋዮች

ወደ ፍርድ ቤት ወይም ፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች ሲሄዱ እንደ አስተርጓሚ ሊያገለግሉ ከሚችሉ ቤተሰቦቻቸው ጋር ካልሆነ በተቋማቱ በኩል የሚደረግላቸው ድጋፍ አለመኖሩን ለመረዳት ተችሏል፡፡

በተጨማሪም በክትትሉ በተሸፈኑ ፍርድ ቤቶች እና ፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች ክስ፣ መልስ እና የመሳሰሉትን ሰነዶች ለዐይነ ስውራን ተደራሽ በሆነ አቀራረብ ማለትም፦ በብሬል፣ በድምፅና በመሳሰሉት አማራጮች እንደማያቀርቡና ከዚህ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶች ተደራሽ በሆነ መልኩ እንዲቀርቡ የሚያስችል አስገዳጅ ተቋማዊ አሠራርም አለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

**የአመለካከት መሰናክሎች**

ክትትል በተደረገባቸው ሁሉም የፍትሕ ተቋማት የሚሠሩ ሠራተኞችና ኃላፊዎች በተደራጀ መንገድ ስለአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ሰብአዊ መብቶች በተለይም የፍትሕ ተደራሽነት ላይ ያተኮረ ስልጠና ወይም የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት አላገኙም፡፡ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን መብቶቻቸውን ከማወቅ እና እንዲከበርላቸው ከመጠየቅ አንጻር የግንዛቤ ክፍተቶች መኖራቸውን እና ጉዳዮች የሚፈጸሙላቸው በፍትሕ ተቋማቱ ቅንነትና ችሮታ እንደሆነ አድርገው እንደሚያስቡ ኮሚሽኑ ተገንዝቧል፡፡

ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው አንዳንድ ዳኞችና ዐቃቤያነ ሕግ የአካል ጉዳተኞችን እና የአረጋውያንን ጥያቄ የሰብአዊ መብቶች ጥያቄ እንደሆነ የሚገነዘቡ ቢሆንም፤ አንዳንዶች ግን ከሰብአዊነት/ከሐዘኔታ አንጻር የሚመለከቱ መሆናቸውን እና በአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን መብቶች ዙሪያ የግንዛቤ ክፍተት ያለ መሆኑን ተመልክቷል፡፡ በተጨማሪም በክትትሉ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው አንዳንድ የፍትሕ ተቋማት ሠራተኞች በቃለ መጠይቅ ወቅት አካል ጉዳተኞችን እና አረጋውያንን ለመግለጽ ክብረ ነክ እና መብትን የሚነኩ አገላለጾችን (derogatory terms) ሲጠቀሙ ተስተውሏል፡፡

## ምክረ ሐሳቦች

- ክትትሉ የተከናወነባቸው እና በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች እና ፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን የሚገጥማቸውን ተቋማዊ መሰናክሎች በማስወገድ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ የሚረዱ አዳዲስ ሕጎችን፣ ፖሊሲዎችን እንዲሁም የአሠራር ሥርዓቶችን እንዲያወጡ እና ክፍተት በታየባቸው ነባር ሕጎች፣ ፖሊሲዎች እና የአሠራር ሥርዓቶች ላይ ተገቢውን ማሻሻያዎች እንዲያደርጉ፤
- ክትትሉ የተከናወነባቸው እና በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች እና ፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን የሚገጥማቸውን ከባቢያዊ ተግዳሮቶች ለማስወገድ በሁሉም መግቢያ በሮች ራምፕ እንዲያስገነቡ፣ በፎቆች ላይ አሳንሰር እንዲያስገጥሙ፣ በምድረ ግቢያቸው ውስጥ ለእንቅስቃሴ እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን እንዲያጸዱ እና ግንባታ ለሚያስፈልጋቸው የማስተካከያ ግንባታ እንዲያደርጉ እንዲሁም የመጸዳጃ ቤቶቻቸውን ተደራሽ ለማድረግ ማሻሻያ ግንባታዎችን እንዲያካሂዱ፤
- ክትትሉ የተከናወነባቸው እና በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች እና ፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ከመረጃ እና ተግባቦት ጋር በተገናኘ የሚገጥማቸውን ተግዳሮት ለማስወገድ በቋሚነት የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ

እንዲቀጥሩ፣ በጊዜያዊነት መስማት ከተሳናቸው ማኅበራት ጋር በቅርበት በመሥራት የትርጉም አገልግሎት ማግኘት የሚችሉበትን ሁኔታ እንዲያመቻቹ፣ በመንቀሳቀሻ ቦታዎች ግልጽ የሆኑ ጠቋሚ ምልክቶችን እንዲያስቀምጡ እንዲሁም ለዐይነ ስውራን ክስ፣ መልስ እና ማናቸውም በቀለም ጽሑፍ የተዘጋጁ የሚመለከቷቸውን ሰነዶች በድምፅ ቅጂ ወይም በብሬል እንዲደርሳቸው በማድረግ ተደራሽነታቸውን እንዲያረጋግጡ፤

- ክትትሉ የተከናወነባቸው እና በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች እና ፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ከአመለካከት ጋር በተገናኘ የሚገጥማቸውን ተግዳሮት ለማስወገድ አመራር እና ሠራተኞችን ጨምሮ ለዳኞች እና ለዓቃብያነ ሕግ የስልጠና ፍላጎትን መሠረት ያደረገ የሰብአዊ መብቶች ስልጠና እንዲሰጣቸው እንዲያደርጉ፤ እንዲሁም ከአመለካከት ጋር በተገናኘ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ላይ የሚደርሱ ጫናዎችን ለመቀነስ ቅሬታ የሚያቀርቡበትን እና አፋጣኝ ምላሽ የሚያገኙበትን ሁኔታ እንዲያመቻቹ፤
- የፍትሕ ሚኒስቴር እና ክትትሉ የተካሄደባቸው ክልሎች የፍትሕ ቢሮዎች በሥራቸው የሚገኙ የፍትሕ ተቋማትን ተቋማዊ፣ ከባቢያዊ፣ የመረጃና ተግባቦት እንዲሁም የአመለካከት ሁኔታ ለማሻሻል የሚያስችል ድጋፍ እና ክትትል እንዲያደርጉ ፤
- ክትትሉ የተከናወነባቸው እና በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች እና ፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን ተካታችነት ለማረጋገጥ የሚያስችል በቂ በጀት መያዙን እንዲያረጋግጡ፤
- የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ የክልል ምክር ቤቶች፣ ገንዘብ ሚኒስቴር እና በየክልሉ የሚገኙ የገንዘብ ቢሮዎች የፍትሕ ተቋማት የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን ተካታችነት ለማረጋገጥ የሚያስችል በቂ በጀት የተመደበላቸው መሆኑን እንዲያረጋግጡ፤
- የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በሁሉም ፍርድ ቤቶች እና የፍትሕ ተቋማት የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ መኖሩን ለማረጋገጥ የሥራ መደቡ እንዲኖር እንዲያደርግ፤
- በዚህ የሰብአዊ መብቶች የክትትል ሥራ ያልተሸፈኑ ነገር ግን መሰል ተቋማዊ፣ ከባቢያዊ፣ የመረጃና ተግባቦት እንዲሁም የአመለካከት ተግዳሮቶች የሚስተዋሉባቸው ሁሉም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች እና የፍትሕ ተቋማት በዚህ ሪፖርት የተሰጡ ምክረ ሐሳቦችን እንዲፈጽሙ።

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ/ኮሚሽኑ) በሕግ ከተሰጡት ሥልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነቶች መካከል የሰብአዊ መብቶች ክትትል ማድረግ አንዱ በመሆኑ፤ በተለይ ለሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ታሳቢ ያደረጉ የክትትል ሥራዎችን ያከናውናል። በዚሁ መሠረት፣ ኮሚሽኑ የፍትሕ ተቋማት አገልግሎቶች ለአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ባላቸው ተደራሽነት ዙሪያ የሰብአዊ መብቶች ክትትል አካሂዷል።

የሰብአዊ መብቶች ክትትሉ ያተኮረው ፍርድ ቤቶች እና ፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች ለአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ያላቸው የተደራሽነት ሁኔታን መገምገም እንደመሆኑ፤ ክትትሉ በተደረገባቸው የፍትሕ ተቋማት ውስጥ የተደራሽነት መብትን አስመልክቶ በአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ላይ የሚደርሱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችና ለአካል ጉዳተኞች የሚደረጉ የተመጣጣኝ/ምክንያታዊ ማመቻቸት እርምጃዎች ያሉበትን ደረጃ ለይቷል።

ክትትሉ የተደረገባቸው ቦታዎች ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ ላይ ተመላክተዋል።

| # | ክትትል የተካሄደባቸው ቦታዎች | ልዩ ቦታ |
|---|---|---|
| 1. | አፋር ክልል | • የአፋር ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት<br>• የሰመራ እና ሎጊያ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት<br>• የአሳይታ ወረዳ ፍርድ ቤት<br>• የአፋር ክልል ፍትሕ ቢሮ<br>• የሰመራ እና ሎጊያ ከተማ ፍትሕ መምሪያ<br>• የአሳይታ ወረዳ ፍትሕ ጽሕፈት ቤት<br>• የሰመራ እና ሎጊያ ከተማ የአካል ጉዳተኞች ማኅበር<br>• የአሳይታ ወረዳ የአካል ጉዳተኞች ማኅበር<br>• የአሳይታ ወረዳ የአረጋውያን ማኅበር |
| 2. | ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል | • የቦንጋ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት<br>• የካፋ ዞን ፍትሕ መምሪያ<br>• የቦንጋ ከተማ ፍትሕ ጽሕፈት ቤት<br>• የካፋ ዞን አንድነት የአካል ጉዳተኞች ጥምረት ማኅበር<br>• ቦንጋ ዙሪያ የአረጋውያንና ጡረተኞች ማኅበር |

| | | |
|---|---|---|
| 3. | ኦሮሚያ ክልል | • የጅማ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት<br>• የበደሌ ወረዳ ፍርድ ቤት<br>• የጅማ ከተማ ፍትሕ ጽሕፈት ቤት<br>• የበደሌ ወረዳ ፍትሕ ጽሕፈት ቤት<br>• የጅማ ከተማ አካል ጉዳተኞች ማኅበር<br>• የበደሌ ከተማ አካል ጉዳተኞች ማኅበር<br>• የቡኖ በደሌ ዞን የአረጋውያንና ጡረተኞች ማኅበር |
| 4. | አማራ ክልል | • የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት<br>• የማዕከላዊ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት<br>• የጎንደር ከተማ አስተዳደር ወረዳ ፍርድ ቤት<br>• የጎንደር ዙሪያ ወረዳ ፍርድ ቤት<br>• የአማራ ክልል ፍትሕ ቢሮ<br>• የማዕከላዊ ጎንደር ዞን ፍትሕ መምሪያ<br>• የጎንደር ከተማ አስተዳደር ወረዳ ፍትሕ ጽሕፈት ቤት<br>• የጎንደር ዙሪያ ወረዳ ፍትሕ ጽሕፈት ቤት<br>• የአማራ ክልል የአካል ጉዳተኞች ማኅበራት ፌዴሬሽን<br>• የአማራ ክልል የአረጋውያን ማኅበር<br>• የጎንደር ከተማ የአካል ጉዳተኞች ማኅበር<br>• የጎንደር ከተማ አረጋውያን ማኅበር |
| 5. | ሶማሊ ክልል | • የሶማሊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት<br>• የፋፈም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት<br>• የጅግጅጋ ከተማ ፍርድ ቤት<br>• የቀብሪበያህ (ካውንስል) ከተማ ፍርድ ቤት<br>• የሶማሊ ክልል ፍትሕ ቢሮ<br>• የሶማሊ ክልላዊ መንግሥት የአካል ጉዳተኞች ፌዴሬሽን<br>• ቀብሪበያህ የአካል ጉዳተኞች ማኅበር<br>• የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ፈንድ አስተዳደር የጅግጅጋ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት<br>• የሶማሊ ክልላዊ መንግሥት ሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ |
| 6. | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል | • የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት<br>• የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት<br>• የአሶሳ ከተማ አስተዳደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት<br>• የባምባሲ ወረዳ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት<br>• የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግሥት ፍትሕ ቢሮ<br>• የባምባሲ ወረዳ ፍትሕ ጽሕፈት ቤት |
| 7. | አዲስ አበባ ከተማ | • በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት<br>• በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት<br>• በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አዲስ ከተማ ምድብ ችሎት<br>• በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት |

| | | |
|---|---|---|
| | | • የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት<br>• በፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የካ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት<br>• በፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ ልደታ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት<br>• በፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ አዲስ ከተማ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት<br>• የፍትሕ ሚኒስቴር ዋና ቢሮ<br>• የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኅበር<br>• የኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኞች ማኅበራት ፌዴሬሽን<br>• የኢትዮጵያ ሥጋ ደዌ ተጠቂዎች ብሔራዊ ማኅበር<br>• አዲስ ሕይወት የዐይነ ሥውራን ማእከል<br>• የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ አካል ጉዳተኞች ማኅበር<br>• የአእምሮ ሕክምና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ማኅበር<br>• የኢትዮጵያ ጡረተኞች እና አረጋውያን ማኅበር |

## የክትትሉ ዓላማ

የዚህ ክትትል ዋነኛ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- በተመረጡ አካባቢዎች የሚገኙ ፍርድ ቤቶችና የፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች በሚሰጡት አገልግሎት አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ከሌሎች ጋር በእኩልነት እንዲገለገሉ አስተማማኝ ሁለንተናዊ (ተቋማዊ፣ ከባቢያዊ፣ የመረጃና የተግባቦት ተደራሽነት እና መብትን መሠረት ያደረገ አመለካከት) ተደራሽነት ስለመኖሩ መገምገም፤
- ፍርድ ቤቶችና የፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች የሚሰጡትን አገልግሎት ደረጃ በመመዘን ፈጣን እና ዘላቂ መፍትሔ የሚሹ ክፍተቶችን መለየት እና የመፍትሔ ሐሳቦች ማቅረብ፡፡

## የክትትሉ ሥነ-ዘዴ

ለዚህ የክትትል ሥራ ኮሚሽኑ የተጠቀማቸው ዋና ዋና የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ቃለ መጠይቅ፣ የመስክ ምልከታ እና ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰነዶች ዳሰሳ ናቸው፡፡

***ሀ) ቃለ መጠይቅ፡-*** በክትትሉ በተሸፈኑ የአፋር፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ የኦሮሚያ፣ የአማራ፣ የሶማሊ፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች እና በአዲስ አበባ ከተማ (ፌዴራል) በሚገኙ የፍትሕ ተቋማት ማለትም በፍርድ ቤቶች ውስጥ ከሚሰሩ ዳኞች፣ ከመዝገብ ቤት እና ከአስተዳደር ሠራተኞች፣ ከፍርድ ቤት ተገልጋይ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች፣ ከዐቃብያነ ሕግ፣ በወንጀል ደርጊት ተጠርጥረው ከተያዙ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች እንዲሁም በአካባቢው ከሚገኙ የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን ማኅበራት እና ከሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳዮች መዋቅር መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን፤ ኮሚሽኑ በጠቅላላው ከ177 ሰዎች (40 ሴቶች እና 137 ወንዶች) ጋር ቃለ መጠይቆችን አድርጓል፡፡ ከእነዚህም መካከል 39 አካል ጉዳተኞች (12 ሴቶች እና 27 ወንዶች) እንዲሁም 20 አረጋውያን (6 ሴቶች እና 14 ወንዶች) በቃለ መጠይቁ ላይ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

**ለ) ምልከታ፡-** በቃለ መጠይቅ በተገኙ መረጃዎች መነሻነት ኮሚሽኑ በፍርድ ቤቶችና የፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች ውስጥ በመዘዋወር በሕንጻዎች እና ምድረ ግቢዎች የመስክ ምልከታ በማድረግ የከባቢያዊ ተደራሽነት ሁኔታ መረጃ አሰባስቧል፡፡

**ሐ) ሰነዶች፡-** በቃለ መጠይቅ እና በመስክ ምልከታ የተገኙ መረጃዎችን ለማጠናከር የፍርድ ቤቶችና የፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች አገልግሎት አሰጣጥ ሒደት፣ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ሁኔታን እንዲሁም አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞችን የተመለከቱ መዝገቦችን በመመልከት ኮሚሽኑ ተጨማሪ ማስረጃዎችን አሰባስቧል፡፡

## የክትትሉ ወሰን እና ጊዜ

የሰብአዊ መብቶች ክትትሉ የተካሄደው በተመረጡ የአፋር፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ የኦሮሚያ፣ የአማራ፣ የሶማሊ፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች እና በአዲስ አባበ ከተማ (ፌዴራል) የሚገኙ 23 ፍርድ ቤቶች እና 18 ፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች ላይ ብቻ እንደመሆኑ፤ በኢትዮጵያ በርካታ ከተሞች ውስጥ አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ የፍትሕ ተቋማትን ሙሉ ገጽታ የሚያሳይ አይደለም፡፡ ክትትሉ ከላይ በተጠቀሱ 6 ክልሎች በሚገኙ የፍትሕ ተቋማት ከታኅሣሥ 17-22 ቀን 2015 ዓ.ም. እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የፌዴራል ፍትሕ ተቋማት ላይ ከታኅሣሥ 24 እስከ ጥር 6 ቀን 2015 ዓ.ም. ተከናውኗል፡፡

በተጨማሪም ምንም እንኳን የፍትሕ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ አካታች የሆነ የሥራ ከባቢን መፍጠር እና በተለይ ራሳቸው አካል ጉዳተኞች ሠራተኛ ሆነው የሚያገለግሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት አንዱ መመዘኛ ቢሆንም ይህ ክትትል አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች ተገልጋይ ሆነው የሚገኙበትን አግባብ ብቻ የቃኘ ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

## አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን የተመለከቱ ቁልፍ ፅንሰ ሐሳቦች

**የአካል ጉዳት** ምን ማለት እንደሆነ የሚያሣይ ዓለም አቀፋዊና ወጥ የሆነ የጋራ ስምምነት የተደረሰበት ትርጓሜ የለም፡፡ ስለዚህ አካል ጉዳተኝነት በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ ሰፊና ውስብስብ ፅንሰ ሐሣብ ነው፡፡ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተ.መ.ድ.) የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት ትርጓሜ መሠረት፡ "አካል ጉዳተኞች" የረዥም ጊዜ አካላዊ፣ አእምሮአዊ፣ ሥነ-አእምሮአዊ ወይም የስሜት ህዋሳት ጉዳቶች ኖሮባቸው በሚያጋጥሟቸው የተለያዩ መሰናክሎች ምክንያት ከሌሎች አቻዎቻቸው ጋር በእኩል ደረጃ በማኅበረሰቡ ውስጥ ሙሉና ውጤታማ ተሳትፎ ማድረግ ያልቻሉ ሰዎችን ያጠቃልላል፡፡

**የአካል ጉዳት ዐይነቶች፡- የስሜት ሕዋሳት ጉዳት ዐይነት** /Sensory Impairments/ ፡- ዐይነ ሥውርነት፣ (በከፊል ወይም በሙሉ አለማየት) ፤ የመስማት የጆሮ፣(በከፊል ወይም በሙሉ አለመስማት)፤ የማሽተት አፍንጫ፣ (ሽታን ወይም ጠረንን አለመለየት) ፣ ከመቅመስ ጋር የተያያዘ የምላስ ጉዳት፤ **የአካላዊ ጉዳት ዐይነት**/ Physical Impairments/፡- ከእጅ፣ እግር፣ ደረት፣ ትከሻ፣ መቀመጫ ጋር የተያያዙ ጉዳቶች፤ **አእምሮአዊ፣ ሥነ-አእምሮአዊ ጉዳት ዐይነት** /Mental, Intellectual Impairments/ ፡- ኦቲዝም፣ ከትምህርትና ከማወቅ፣ አካባቢን ከመገንዘብ ጋር የተዛመደ፣ ጽሑፍን ከተለመደው በተለየ ሁኔታ መገንዘብ፣ ምሳሌ፡- ወደጎን በመገልበጥ፣ በመዘቅዘቅ መጻፍ፣ ሌሎች በጣም ሰፊና ስምምነት ያልተደረሰባቸው ጉዳቶችንም ያካትታል፡፡

**የአረጋዊነትን ፅንሰ ሐሳብ** በልዩ ልዩ መንገዶች ትርጉም ለመስጠት የተሞከረ ሲሆን፤ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለስታትስቲካዊ ዓላማ የሚጠቀምበት ትርጉም ከውልደት አንስቶ ያለውን የዕድሜ ዘመን (Chronological age order) መሠረት በማድረግ ዕድሜያቸው 60 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን የሚያጠቃልል ነው፡፡ በተለያዩ የሕግና የፖሊሲ ሰነዶች የዕድሜ ዘመንን መሠረት ካደረጉ ትርጓሜዎች ባሻገር የጡረታ መውጫ ዕድሜን (Retirement age) ወይም የዐቅምና ጤና መታወክን (Functional age) መሠረት በማድረግ ትርጉም ሊሰጠውም ይችላል፡፡

**"ተደራሽነት"**፡- ማለት አካል ጉዳተኞች ኑሯቸውን በነጻነት እንዲመሩና በሁሉም የሕይወት ዘርፍ የተሟላ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ለማስቻል አካል ጉዳተኞች ከሌሎች ጋር በእኩል ደረጃ የሚኖሩበት ቁሳዊ ከባቢ፣ መጓጓዣ፣ የመረጃና ግንኙነት ቴክኖሎጂዎችና ሥርዓቶችን ጨምሮ የመረጃና ግንኙነቶች፣ በከተማም ይሁን በገጠር ለሕዝብ ክፍት የሆኑ ወይም ሕዝብ የሚጠቀምባቸው ተቋማትና አገልግሎቶች ተደራሽ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተገቢ እርምጃዎችን መውሰድና የተደራሽነት እንቅፋቶችንና መሰናክሎችን መለየት እና ማስወገድን ያጠቃልላል፡፡

**የመሰናክሎች ዐይነቶች፡- *"ተቋማዊ መሰናክሎች"*፡-** ኢ-ፍትሐዊ ፖሊሲዎች፣ አካሄዶች ወይም ተግባራት ናቸው፡፡ ተቋማዊ መሰናክል ብዙውን ጊዜ ሳይታሰብ የሚቀመጥ አካል ጉዳተኞችን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዳይሳተፉ የሚከለክል እና አድልዎ የሚያደርግ ሁኔታ ነው፡፡

**"ከባቢያዊ መሰናክሎች"፡-** የሕዝብ መገልገያ ሕንጻዎችንና ቦታዎችን፣ የሥራ፣ መንገዶች እና የመንገድ መወጣጫዎች፣ የመኪና ማቆሚያዎች፣ አሳንሰሮች፣ አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቶች፣ መግቢያዎች፣ የመጸዳጃ ቤቶች፣ ወዘተ አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ሳይደረጉ ሲገነቡ ነው፡፡

**“የመረጃና ተግባቦት መሰናክሎች”፦** የቃል ንግግሮችን፣ የሚታዩ ምልክቶችን፣ ብሬልን፣ በዳሰሳ የሚደረስባቸውን የግንኙነት ዘዴዎች፣ ጉልህ ሕትመቶችን፣ ምቹና ዘርፈ ብዙ የብዙኃን መገናኛ ዘዴዎችን፣ የተጻፉና የተቀረጹ ድምጾችን፣ ግልጽ ቋንቋዎችን እና የሰው አንባቢ እንዲሁም በየጊዜው እየተሻሻሉ የሚሄዱና አማራጭ የተግባቦት ስልቶችንና የመረጃ ማቅረቢ ዘዴዎችን ለአካል ጉዳተኞች በፍላጎታቸው መሠረት ተደራሽ አለማድረግን ያጠቃልላል፡፡ የመረጃና ተግባቦት ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ለምሳሌ፣ በፍትሕ ተቋማት ለዐይነ ስውራን ተገልጋዮች ብሬል፣ ትልቅ ሕትመት፣ ወይም ኦዲዮ መረጃ ማመቻቸት እንዲሁም መስማት ለተሳናቸው ተገልጋዮች የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ እንዲገኝ ወይም የጽሑፍ መልእክት እንዲለዋወጡ ማመቻቸትን ያካትታል፡፡

**“የአመለካከት መሰናክሎች”፦** የአመለካከት መሰናክሎች በአካል ጉዳተኞች ላይ አድልዎ የሚያደርጉ ባሕሪያት፣ አመለካከቶች፣ ፍረጃዎች እና የተሳሳቱ ግምቶች ናቸው፡፡ እነዚህ መሰናክሎች ብዙውን ጊዜ ከቸልታ ወይም ከተሳሳተ ግንዛቤ ይመነጫሉ፡፡

**“ተመጣጣኝ ማመቻቸት”፦** ማለት አካል ጉዳተኞች ሁሉንም ሰብአዊ መብቶችና መሠረታዊ ነጻነቶች ከሌሎች ጋር በእኩል ደረጃ ማጣጣምን ወይም መጠቀምን ለማረጋገጥ፣ እንደ አስፈላጊነቱ፣ የሚደረግና ያልተመጣጠነ ወይም ያልተገባ ጫና የማይፈጥር አስፈላጊና ተገቢ የሆነ ለውጥና ማስተካከያዎች ነው፡፡

**“ሁሉን አቀፍ ንድፍ”፦** ማለት ተጨማሪ የማስማማት እርምጃ ወይም የተለየ ንድፍ ሳያስፈልግ፣ የሚቻል እስከሆነ ድረስ፣ ምርቶችን፣ ከባቢዎችን፣ መርኃ ግብሮችንና አገልግሎቶችን ማንኛውም ሰው በእኩል ጥቅም ላይ እንዲያውሉ አድርጎ መንደፍ ነው፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ ሁሉን አቀፍ ንድፍ የተወሰኑ አካል ጉዳተኞች የሚጠቀሙባቸው ተስማሚ መሣሪያዎችን ማስቀረት የለበትም፡፡

## የፍትሕ ሥርዓት ተደራሽነት የሕግ ማዕቀፎች እና መርሖች

ይህ የፍትሕ ሥርዓት ተደራሽነት የሰብአዊ መብቶች ክትትል የተከናወነው የአካል ጉዳተኞችንና አረጋውያንን መብቶች በተመለከተ ያሉ ዓለም አቀፍ፤ አህጉራዊና ብሔራዊ የሕግ ማዕቀፎችን እና መርሖችን መነሻ በማድረግ ነው፡፡

## ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች

ሁሉን አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ (Universal Declaration of Human Rights) ማንኛውም ሰው በሀገሪቱ ሕገ መንግሥት ወይም በሕግ ዕውቅና በተሰጣቸው መሠረታዊ ነጻነቶች ላይ የሚፈጸም ጥሰትን በተመለከተ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል በማቅረብ የተሟላ ፍትሕ ወይም ውጤታማ መፍትሔ የማግኘት መብት እንዳለው ዕውቅና ይሰጣል፡፡[1] የተባበሩት መንግሥታት ዋና ዋና የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችም ፍትሕ የማግኘት መብትን አስመልክቶ የተለያዩ ድንጋጌዎችን አካተዋል፡፡ ለአብነት የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን እንደሚደነግገው የመብት ወይም የመሠረታዊ ነጻነት ጥሰት የደረሰበት አካል የተሟላ ፍትሕ

[1] ሁሉን አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ፣ አንቀጽ 8

ወይም ውጤታማ መፍትሔ ማግኘት እንዳለበትና ማንኛውም ሰው በሕግ ፊት እኩል እንደሆነ ይደነግጋል።[2]

በተ.መ.ድ. የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት አንቀጽ 12 መሠረት ተዋዋይ መንግሥታት *(1) አካል ጉዳተኞች በሕግ ፊት በሁሉም ቦታ እንደ ሰው ዕውቅና የማግኘት መብት እንዳላቸው ዳግም ማረጋገጣቸውን፤ (2) በሁሉም የሕይወት ዘርፎች ከሌሎች ጋር በእኩል ደረጃ የሚገለገሉበት ሕጋዊ ችሎታ እንዳላቸው ዕውቅና መስጠት ያለባቸው መሆኑን ፤ (3) ሕጋዊ ችሎታቸውን ለመገልገል የሚጠይቁትን ድጋፍ ለማቅረብ አግባብነት ያለውን እርምጃ ሁሉ መውሰድ ያለባቸው መሆኑን ፤ እና (4) ከሕጋዊ ችሎታ አጠቃቀም ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሁሉም እርምጃዎች በዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች ሕግ መሠረት ያልተገባ መገልገልን ለመከልከል ተገቢና አስተማማኝ ከለላዎችን የሚሰጡ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያለባቸው መሆኑን ይደነግጋል።*
በተጨማሪም በስምምነቱ አንቀጽ 13(1 እና 2) ላይ እንደተቀመጠው ተዋዋይ መንግሥታት *“አካል ጉዳተኞች በምርመራና ሌሎች በቅድመ-ምርመራ ደረጃዎች ሳይቀር የሕግ ክርክር በሚካሄድባቸው ጊዜያት ሁሉ ለምስክርነት መቆምን ጨምሮ በቀጥታም ሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ያላቸውን የተሳትፎ ሚና ለማመቻቸት፣ ሥነ-ሥርዓታዊና ከዕድሜ ጋር የተገናዘቡ ድጋፎች በማቅረብ ጭምር፣ አካል ጉዳተኞች ከሌሎች ጋር በእኩል ደረጃ አስተማማኝ የፍትሕ አገልግሎት ማግኘታቸውን ተዋዋይ መንግሥታት ማረጋገጥ አለባቸው። የአካል ጉዳተኞችን ፍትሕ የማግኘት መብት ለማረጋገጥ ተዋዋይ መንግሥታት ለፖሊስና ማረሚያ ቤቶች ሠራተኞች ጨምሮ በፍትሕ አስተዳደር ሥራ ላይ ለተሠማሩ ሰዎች የሚሰጠውን ተገቢ ሥልጠና ማስፋፋት አለባቸው።”*

## አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ሕጎች

የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የአረጋውያን መብቶች ፕሮቶኮል አንቀጽ 4 አባል ሀገራት አዳዲስ ሕጎችን በማውጣት እና ነባር ሕጎችን በማሻሻል ለአረጋውያንን እኩል አያያዝ እና ጥበቃን የማረጋገጥ፤ አረጋውያን የሕግ ድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ መብቶቻቸው እንዲጠበቁ ማድረግ፤ እንዲሁም በፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ላሉ ሁሉም አካላት ስልጠና እንዲወስዱና በአግባቡ ሕጎችና ፖሊሲዎችን እንዲተረጎሙ እና እንዲተገበሩ በማድረግ የአረጋውያንን መብቶች እንዲጠበቁ የማድረግ ኃላፊነት እንዳለባቸው ይደነግጋል።

የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የአካል ጉዳተኞች መብቶች ፕሮቶኮል በአፍሪካ ኅብረት ሠላሳኛው የመሪዎች ጉባኤ በጥር 21 ቀን 2010 ዓ.ም. የጸደቀ አህጉራዊ የሕግ ማዕቀፍ ሲሆን እስከአሁን 15 የኅብረቱ አባል ሀገራት ባለመፈረማቸው አስገዳጅ አልሆነም። ኢትዮጵያም ይህን ሕግ አልፈረመችም። የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የአካል ጉዳተኞች መብቶች ፕሮቶኮል ዋና ዓላማ በአፍሪካ ውስጥ የአካል ጉዳተኞችን የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ማስፋፋት፣ መጠበቅ እና ተፈጥሯዊ ክብራቸው መከበሩን ማረጋገጥ ነው። ፕሮቶኮሉ የተ.መ.ድ. የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት ዕሴቶችና መርሖች ጋር በተጣጣመ መልኩ በአፍሪካ የሚኖሩ አካል ጉዳተኞችን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ያስገባ ነው።

[2] የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን፣ አንቀጽ 14

# ብሔራዊ ሕጎች

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢ.ፌ.ዴ.ሪ.) ሕገ መንግሥት በምዕራፍ ሦስት ሥር ከዘረዘራቸው ሰብአዊ መብቶች በተጨማሪ፣ ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች የሀገሪቱ ሕግ አካል እንደሆኑና[3] በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የተካተቱ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች ከዓለም አቀፋ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ መርሖች እንዲሁም ሀገሪቱ ከተቀበለቻቸው የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ መተርጎም እንዳለባቸው ይደነግጋል።[4] ስለሆነም፤ ቀደም ባለው ክፍል በዓለም አቀፍ እና አህጉር አቀፍ ስምምነቶች ውስጥ የተጠቀሱት የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን መብቶች በሙሉ የኢትዮጵያ ሕግ አካል በመሆናቸው ሊጠበቁላቸው፣ ሊከበሩላቸው እና ሊሟሉላቸው ይገባል።

ሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ 25 ስለ እኩልነት መብት ሲዘረዝር "ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው፤ በመካከላቸውም ማንኛውም ዐይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል። በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግባቸው ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው" በማለት ይደነግጋል። በዚህ አንቀጽ ላይ በግልጽ በአካል ጉዳት እና በዕድሜ ምክንያት ልዩነት መደረግ እንደሌለበት ባይገልጽም "በሌላ አቋም ምክንያት" የሚለው ሐረግ አካል ጉዳትን እና ዕድሜንም እንደሚጨምር መረዳት ያስፈልጋል።

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37(1) ፍትሕ የማግኘት መብት እንደተመለከተው ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው።

በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ 1234/2013 አንቀጽ 19(1፣ ሰ) ሥር የፌዴራል ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶች *"የጾታዊ ጥቃት የተፈጸመባቸው ሴቶች፣ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋውያንን አስመልክቶ በፍርድ ቤቶች የሚከፈቱ መዝገቦች በተፋጠነ ፍትሕ አገልግሎት እልባት እንዲያገኙ እና የሕግ ባለሙያ ድጋፍ"* እንዲሰጣቸው ይደርጋሉ። በተጭማሪም በአዋጁ በአንቀጽ 31(3) ሥር *"የምልክት ቋንቋ ለሚጠቀም አካል ጉዳተኛ በተመሳሳይ የምልክት ቋንቋ ችሎታ ያለው ባለሙያ ይመደብለታል"* በሚል ተደንግጓል።

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የመንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 ሁሉም የመንግሥት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን የእኩል እድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ የማድረግና አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ የማድረግ ግዴታ አለባቸው በማለት ይደነግጋል።

ከላይ ከተመለከትናቸው ብሔራዊ ሕጎች በተጨማሪ የአካል ጉዳተኞችን መብት በተመለከተ ካሉ ሕጎች ውስጥ አንዱ የኢትዮጵያ ሕንጻ አዋጅ ቀጥር 624/2001 ነው። ይህ አዋጅ በሀገሪቱ ውስጥ

[3] የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት፣ አንቀጽ 9(4)
[4] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 13(2)

የሚገነቡ ሕንጻዎች ማሟላት ስላለባቸው አጠቃላይ ግዴታዎች ያስቀመጠ ሲሆን፣ በአንቀጽ 36 ሥር የሚገነቡት ሕንጻዎች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ ሊሆኑ እንደሚገባቸው ይደነግጋል።

የአካል ጉዳተኞች የሥራ ሥምሪት መብት አዋጅ ቁጥር 568/2000 ሀገሪቱ ከምትከተለው እኩል የሥራ ዕድል መርሖ ጋር የሚጣጣም፤ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ የሥራ ሁኔታ የሚፈጥርና በሥራ ሥምሪት የሚዲርስባቸውን መድልዎ በፍርድ መድረኮች በቀላሉ ለማስረዳት የሚያስችል አሠራር የሚዘረጋ አዲስ ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የወጣ አዋጅ ነው።

## አግባብነት ያላቸው ዓለም አቀፍ መርሖች

በተ.መ.ድ. የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት አንቀጽ 3 የተዘረዘሩት **ስምንት አጠቃላይ መርሖች**[5] በስምምነቱ ውስጥ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎችን ለመረዳት እና ለመተርጎም መመሪያ ናቸው። ተዋዋይ መንግሥታት ብሔራዊ ሕጎችን፣ ፖሊሲዎችን፣ አሠራሮችን በማዘጋጀትና በመተግበር ሂደት ውስጥ እነኚህን አጠቃላይ መርሖች ከግምት የማስገባት ግዴት አለባቸው።

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የተዘጋጀው የአካል ጉዳተኞች የፍትሕ ተደራሽነት ዓለም አቀፍ መርሖች እና መምሪያዎች (International Principles and Guidelines on Access to Justice for Persons with Disabilities)[6] ለፍትሕ ተቋማት ፣ ለብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት እና የሲቪክ ማኅበራት (የአካል ጉዳተኞች ማኅበራትን) የግንዛቤ ማስፋፋት ተግባራትን፣ ስልጠናዎችን እና ተመጣጣኝ ማመቻቸትን ለማጠናከር እንዲሁም አካል ጉዳተኞች በፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ውጤታማ ለማድረግ አግባብነት ያላቸውን እርምጃዎችን ያካተተ ሰነድ ነው።

ተ.መ.ድ. ጠ.ጉ.ም. በ1991 በመንግሥታቱ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ቁጥር 46/91 አማካኝነት **የአረጋውያን መርሖችን** አጽድቋል። ይህ የመርሖች ስብስብ በሌሎች የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች የተጠቀሱ መብቶችና ነጻነቶችን ዳግም ለማጽናት የሚያግዝ ማዕቀፍ ነው። የተ.መ.ድ. የአረጋውያን መርሖች ስብስብ አምስት መሠረታዊ መርሖች ያሉት ሲሆን፤ እነሱም፡- ነጻነት (Independence)፣ ተሳትፎ (Participation)፣ እንክብካቤ (Care)፣ ራስን መቻል (Self-fulfillment) እና ክብር (Dignity) ናቸው። እያንዳንዱ መርሖች አረጋውያን የሕይወት እና አካላዊ ደኅንነት መብት፣ በቂ ምግብ፣ ውሃ፣ መጠለያ፣ አልባሳት እና የጤና እንክብካቤ የማግኘት መብት፣ ትምህርትና ስልጠና የማግኘት መብት፣ የሥራ ዕድሎች መብት፣ በማኅበረሰብ ጉዳዮች ውስጥ ተሳትፎ የማድረግ መብት፣ የኢኮኖሚ እና የባህል መብቶችን የተመለከቱት ሁሉም ሰብአዊ መብቶቻቸው ተከብረው እና ተፈጥሯዊ ክብራቸው ተጠብቆ የመኖር መብት ያላቸው መሆኑን ያጸናሉ።

[5] (1)ተፈጥሯዊ ክብርን፣ የራስን ምርጫ የማድረግ ነጻነትን ጨምሮ ግለሰባዊ ልዕልና እና ሰብአዊ ነጻነትን ማክበር፤ (2) አድሏዊ ልዩነት አለማድረግ፤ (3) ሙሉና ውጤታማ ተሳትፎና ኅብረተሰባዊ ተካታችነት፤ (4) ልዩነትን ማክበርና አካል ጉዳተኞች የብዝኃነትና የሰብአዊነት አካል መሆናቸውን መቀበል፤ (5) የዕድል እኩልነት፤ (6) ተደራሽነት፤ (7) የወንዶችና የሴቶች እኩልነት፤ እና (8) የአካል ጉዳተኛ ሕፃናትን እያደገ የሚሄድ ችሎታ ማክበር እና የአካል ጉዳተኛ ሕፃናት ማንነታቸውን የመጠበቅ መብታቸውን ማክበር ናቸው።

[6] https://social.desa.un.org/sites/default/files/migrated/15/2020/10/Access-to-Justice-EN.pdf

# ክፍል ሦስት

## የክትትሉ ግኝቶች

በዚህ የሪፖርቱ ክፍል ክትትሉ የተከናወነባቸው የፍትሕ ተቋማትና ቦታዎች የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን የሰብአዊ መብቶች አጠባበቅ ሁኔታ በአራት ንኡስ ክፍሎች ማለትም የተቋማዊ፣ የከባቢያዊ፣ የመረጃና ተግባቦት ተደራሽነት እንዲሁም የአመለካከት መሰናክሎችን በተመለከተ የክትትሉ ግኝቶች ቀርበዋል፡፡

## ተቋማዊ ተደራሽነት

**የአፋር ክልል ፍትሕ ተቋማት**: በክትትሉ በተሸፈኑት የአፋር ክልል ፍርድ ቤቶች እና የፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች አካል ጉዳተኞችንና አረጋውያንን ከማካተት አንጻር አካል ጉዳተኞችና አረጋውያንን ታሳቢ ያደረገ የበጀት ዕቅድ፣ ፖሊሲ ወይም መመሪያ አለመኖሩን እንዲሁም የአካል ጉዳተኞችና አረጋውያንን ፍላጎቶች መሠረት ያደረገ የአሠራር ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑን ተረድቷል፡፡

ክትትል በተካሄደባቸው የፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል አካል ጉዳተኞችን፣ አረጋውያንን እና ሌሎች ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ያማከለ ነጻ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት፣ በጠበቆች በነጻ መወከል እንዲሁም የንቃተ ሕግ የግንዛቤ ማስፋፊያ የአሠራር ሥርዓት የተዘረጋ ቢሆንም፤ በትግበራ ሂደቱ ላይ በተለይም ክትትል በተደረገባቸው የወረዳ የፍትሕ ተቋማት አሠራሩ ወጥነት እንደሌለው እና በአንዳንድ ቦታዎች አገልግሎቱ እንደማይሰጥ በክትትሉ ተለይቷል፡፡ ለአብነት በአሳይታ ወረዳ ፍትሕ ጽሕፈት ቤት በጠበቆች በነጻ የመወከል እና ነጻ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ባለመኖሩ ተገልጋዮች በሰመራ ከተማ ወደሚገኙ የፍትሕ ተቋማት በመሄድ አገልግሎቱን የሚያገኙ በመሆኑ በጉዞ እንግልት እንደሚደርስባቸው ኮሚሽኑ ተገንዝቧል፡፡

በተጨማሪም ከሕፃናት አካል ጉዳተኞች ጥቃት ጋር በተያያዘ ክርክር ሲደረግ እና ምስክር ሲሰማ ዕድሜያቸውን እና አካል ጉዳታቸውን ያማከለ የአሠራር ሥርዓት አለመኖሩን ከፍትሕ ቢሮ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡ በተጨማሪም ሴት አካል ጉዳተኞችን እና አረጋውያንን አስመልክቶ ተደራራቢ የመብት ጥሰት ተጋላጭነታቸውን ከግምት ያስገባ የአሠራር ሥርዓት አለመዘርጋቱን ኮሚሽኑ ለማወቅ ችሏል፡፡

**የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ፍትሕ ተቋማት፡** የክልሉ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 25 (1) ሥር "ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው፤ በመካከላቸውም ማንኛውም ዐይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሀይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ *በአካል ጉዳተኝነት፣* በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩል እና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው" በማለት የሚደነግግ መሆኑን ኮሚሽኑ መልካም ተሞክሮ መሆኑን ተግንዝቧል፡፡

በክትትሉ የተሸፈኑ የፍትሕ ተቋማት አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ተገልጋዮችን የሚያስተናግዱ ባለሙያዎችን በመመደብ የጽሑፍ አገልግሎት (የክስ፤ የመልስ፤ የይግባኝ፤ እና

የማመልከቻ ጽሑፍ) ቅድሚያ በመስጠት እንዲሁም የፍትሕ ተቋማቱ የተቋማቸውን ከባቢያዊ ተደራሽነት ለማሻሻል በስትራቴጂክ ዕቅዳቸው ውስጥ በማካተት እየሠሩ መሆኑን የተቋማቱ ኃላፊዎች አስረድተዋል። በፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ላይ ለአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ነጻ የሕግ አገልግሎት ድጋፍ፤ ክስ ለመመስረት ነጻ የጽሑፍ አገልግሎት እና በጠበቆች በነጻ የመወከል ሁኔታ መኖሩን ኮሚሽኑ የተገነዘበ ሲሆን በወንጀል ጉዳዮች ተከሰው ለሚቀርቡ አካል ጉዳተኛ እና አረጋውያን ተጠርጣሪዎችም ተከላካይ ጠበቃ የሚመደብበት አሠራር መኖሩን የተገኘው መረጃ ያሳያል። በሌላ በኩል በፍትሕ ተቋማቱ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞችን የሚያካትት የጽሑፍ ፖሊሲ እና መመሪያ እንዲሁም የፋይናንስ ዕቅድ አለመኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል።

**የኦሮሚያ ክልል ፍትሕ ተቋማት**፡ የኦሮሚያ ክልል መንግሥት ፍርድ ቤቶች አደረጃጀት፣ ሥልጣን እና ተግባር እንደገና ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 216/2011 በአንቀጽ 5(1) ሥር የክልሉ ፍርድ ቤቶች "*በፌዴራሉና በክልሉ ሕገ-መንግሥት የተደነገጉ የግልና የጋራ መብትና ነጻነቶችን ማስከበር*" ዓላማ እንዳላቸው ይደነግጋል።

ኮሚሽኑ ክትትል ባከናወነባቸው ፍርድ ቤቶችና የፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን መብቶችን አካቶ የወጣ የጽሑፍ ፖሊሲ እና መመሪያ እንደሌለ የተገኘው መረጃ ያሳያል። በክትትሉ ፍትሕ ተቋማት አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ተገልጋዮችን የሚያስተናግዱ ባለሙያዎችን በመመደብ የጽሑፍ አገልግሎት በመስጠት፤ ሲመጡ ቅድሚያ በመስጠት እና በስትራቴጂክ ዕቅዳቸው ውስጥ በማካተት እየሠሩ መሆኑን አስረድተዋል። ክትትል በተደረገባቸው የፍትሕ ተቋማት በፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ላይ ለአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ነጻ የሕግ አገልግሎት ድጋፍ፤ ክስ ለመመስረት ነጻ የጽሑፍ አገልግሎት እንዲያገኙ፤ የግል ጠበቆች በነጻ ጥብቅና እንዲቆሙላቸው እንዲሁም በወንጀል ጉዳዮች ተከሰው ሲቀርቡ ተከላካይ ጠበቃ እንደሚመደብላቸው የተገኘው መረጃ ያሳያል።

አንድ የ14 ዓመት ታዳጊ ከ5 ዓመት በፊት በመኪና አደጋ በእግሮቹ ላይ ጉዳት በመድረሱ ከትምህርቷ እንደተስተጓጎለች እና ጉዳቱን ያደረሰው ግለሰብ በሕግ ተጠያቂ እንዲሆን፣ ተጎጂም ካሳ እንዲያገኝ ክስ ተመስርቶ የነበረ ቢሆንም የበደሌ ወረዳ ፍትሕ ጽሕፈት ቤትና የተጎጂ ወላጆች ተጎጂ ፍትሐዊ ዳኝነት አግኝቷል ብለው የማያምኑ መሆኑን በሰብአዊ መብቶች ክትትሉ ወቅት ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

**የአማራ ክልል ፍትሕ ተቋማት፡** በየደረጃው ያሉ የአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች እና የፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች አካል ጉዳተኞችንና አረጋውያንን ከማካተት አንጻር ለአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ተብሎ የተቀመጠ የበጀት ዕቅድ፣ ፖሊሲ ወይም መመሪያ የላቸውም። ከዚህ በተጨማሪ የፍትሕ ተቋማት የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ምክር ቤት ያወጣውን የአካቶ መመሪያ ቁጥር 40/2012 የመተግበር ግዴታ ያለባቸው በመሆኑ አካል ጉዳተኞችና አረጋውያንን ጉዳይ በዕቅዳቸው አካተው ተግባራትን እንደሚያከናውኑ እንዲሁም ዕቅዳቸው ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ መደረጉን በሪፖርትና በግምገማ መልኩ እንደሚያረጋግጡ ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

ኢሰመኮ ከክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዕቅድ ዳይሬክቶሬት ባገኘው መረጃ መሠረት በ2014 ዓ.ም. በአማራ ክልል ቅድሚያ አገልግሎት ያገኙ አካል ጉዳተኞች ቁጥር ወንድ 2,663 ፣ ሴት 1,840 በድምሩ 4,503 ሲሆኑ፤ አረጋውያን ወንድ 11,835፣ ሴት 8,874 በድምሩ 20,709 ናቸው።

በክትትሉ የተሸፈኑ ፍርድ ቤቶች አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ባለጉዳይ ሆነው በሚሄዱበት ወቅት መዝገባቸው ሲከፈት ልዩ ምልክት ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ እንደሚገባና ችሎቱም ምድር ቤት እንደሆነ፣ ቀጠሮዎች እንዲያጥሩ እና የሕግ ድጋፍ የሚፈልጉ ከሆነም ወደ ፍትሕ ጽሕፈት ቤት እንዲላኩ የሚያስችል አሠራር በዕቅዶቻቸው ላይ አካተው እንደሚሠሩ አስረድተዋል፡፡

ፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች ለጉዳት ተጋላጭ ለሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ነጻ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ይሰጣሉ ወይም ጠበቆች ድጋፍ እንዲሰጡ ያደርጋሉ፡፡ በዚህ መሠረት ከክልሉ ፍትሕ ቢሮ በ2014 ዓ.ም. ወንድ 334 ሴት 222 በድምሩ ለ556 አረጋውያን እና ወንድ 1,282 ሴት 122 በድምሩ ለ1,404 አካል ጉዳተኞች ነጻ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ያገኙ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

በክልል ደረጃ ፍትሕ ቢሮ የሰብአዊ መብቶች ዳይሬክቶሬት ያቋቋመ በመሆኑ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ሲፈጸም ፖሊስ ምርመራ እንዲያደርግ ትዕዛዝ ይሰጣል በጋራም ምርመራውን ያካሂዳል፡፡ ከሕፃናትና ከሴቶች ጥቃት ጋር በተያያዘ ክርክር ሲደረግ እና የምስክር ቃል ሲሰጥ በማኅበራዊ ባለሙያዎች አማካኝነት ለተበዳዮች ወይም ሕጻናትን ጨምሮ አገልግሎቱ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች የምክርና የሥነ ልቦና ማረጋጋት ሥራ ይከናወናል፡፡ ሆኖም ሴቶችና ሕጻናትን ጨምሮ በልዩ ሁኔታ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን በተመለከተ ለጉዳዩ ትኩረት እንደሚሰጠው ከመግለጽ ባሻገር እነዚህን የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚያስተናግዱበት የተለየ አሠራር አለመኖሩን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በጎንደር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት የገንዘብ ክርክር ያላቸው አረጋዊት ከሌሎች የተለየ ለአረጋውያን ተብሎ የተዘረጋ የአሠራር ሥርዓት እንደሌለና ሌላው ማኅበረሰብ በሚጠቀምበት መደበኛ ሥርዓት መስተናገዳቸውን ኮሚሽኑ ባነጋገራቸው ወቅት አስረድተዋል፡፡

**የሶማሊ ክልል ፍትሕ ተቋማት፡** ክትትሉ የተደረገባቸው የክልሉ ፍርድ ቤቶች እና ፍትሕ ቢሮ ለአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ያላቸውን ተቋማዊ ተደራሽነት አስመልክቶ ፖሊሲ ወይም መመሪያ እንዲሁም ዓመታዊ በጀት የላቸውም፡፡ በሶማሊ ክልል የፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 206/2013 ስለ አጠቃላይ ተደራሽነት በአንቀጽ 9(1) የተጠቀሰ ቢሆንም የተደራሽነት ፅንሰ ሐሳብ ትርጓሜ አልተሰጠውም፡፡ ምንም እንኳ በጽሑፍ የተቀመጠ ነገር ባይኖርም በክትትሉ የተሸፈኑ ፍርድ ቤቶች በሰጡት መረጃ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን ጨምሮ ለመብት ጥሰት ተጋላጭ ለሆኑ የኅብረተሰቡ ክፍሎች በአሠራር ደረጃ ቅድሚያ እንደሚሠጣቸው እና በተቻለ መጠን ጉዳያቸው ቶሎ እንደሚታይ አስረድተዋል፡፡

በክልሉ የፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 206/2013 በአንቀጽ 25 ላይ እንደተጠቀሰው ማንኛውም ሰው ጠበቃ የማቆም እንዲሁም የነጻ ሕግ አገልግሎት የማግኘት መብት አለው፡፡ በፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ላይ በክልሉ የጥብቅና አገልግሎት ሰጪዎች ላይ በሚደረግ የግዳጅ የነጻ አገልግሎት የተወሰነ ሰዓት የነጻ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ ከዚህ በተቃራኒው በቀብሪበያ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት የተገኘው መረጃ የሚያመላክተው በወረዳው ፍርድ ቤት ይህ አሠራር እንደሌለ እና እንደዚህ ያሉ ጉዳዮች ጅግጅጋ ወደሚገኙ ፍርድ ቤቶች እንደሚተላለፉ ገልጸዋል፡፡ የአእምሮ ሕመም ወይም አእምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ባለጉዳዮች ሕጋዊ ችሎታ የላቸውም በሚል ጉዳያቸው በወኪሎቻቸው በኩል እንዲፈጸም እንደሚደረግ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የክልሉ አካል ጉዳተኞች ፌዴሬሽን ውል እና ማስረጃ ለአካል ጉዳተኞች ቅድሚያ አገልግሎት እንደሚሰጥ እና አገልግሎቱም በአንጻሩ የተቀላጠፈ እንደሆነ አስረድቷል፡፡

በሶማሊ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 206/2013 አንቀጽ 24 ከሕፃናት ጋር የተገናኘ የፍርድ ሂደት በዝግ ችሎት መደረግ እንደሚችል ይገልጻል። በዚህም መሠረት አካል ጉዳተኛ ሕጻናትን ጨምሮ ሕፃናትን የሚመለከት ጉዳይ በዝግ ችሎት እንደሚታይ እና ዳኞችም ሆኑ ዐቃቤያነ ሕግ የችሎት ክብር ልብስ/ካባ ሳይለብሱ የፍርድ ቤትን የተለመደ አቀራረብ እና ሥነ ሥርዓት ባልጠበቀ መልኩ ለሕፃናት በማይከብድ ሁኔታ እንደሚካሄድ ለማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም በጠቅላይ ፍርድ ቤት እና በጅግጅጋ ከተማ ፍርድ ቤት ለሕፃናት ታስቦ የተለየ ክፍል ተዘጋጅቷል። ይህ ክፍል ለሕፃናት ብቻ ታስቦ የተዘጋጀ እና የባለሙያ ድጋፍም የሚሰጥበት በመሆኑ አካል ጉዳተኛ ሕፃናትም ይስተናገዱበታል። በሌላ በኩል ከቀብሪበያህ (ካውንስል) ከተማ ፍርድ ቤት የተገኘው መረጃ እንደዚህ ዐይነት አሠራር እንደሌለ እና የሕፃናት ችሎትም ሆነ

ለሕፃናት በአጠቃላይ የተለየ አሠራር አለመኖሩን ያስረዳል። አንድ ጉዳይ በዝግ ችሎት የሚታይበት ሁኔታን አስመልክቶ በክልሉ ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 206/2013 አንቀጽ 24 በንዑስ አንቀጽ (ለ) ለማኅበረሰብ ወግና የተከራካሪ ወገኖች ግላዊ ኑሮ ለመጠበቅ አስፈላጊ መሆኑ ከታመነበት እንደሆነ ይደነግጋል። በዚሁ መሠረት ጾታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን የሚመለከቱ ጉዳዮች በዝግ ችሎት የሚታዩበት ሁኔታ እንዳለ ከጠቅላይ ፍርድ ቤት የሴቶች እና ሕፃናት ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ለመረዳት ተችሏል። በተጨማሪም ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ዐቃቢያነ ሕግ ይህንኑ አስረድተዋል። እንደ ሁኔታው አግባብነት ባለው መልኩ እና ሕግን በማይጥስ መልኩ የችሎት አካሄድ ሊቀየር እና ተመጣጣኝ ማመቻቸትም ሊደረግ እንደሚችል ገልጸዋል።

በክትትሉ የተሸፈኑ አራት ፍርድ ቤቶች ኃላፊዎች የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን መብቶች ጉዳይ በፍርድ ቤቶች ዕቅድ ውስጥ ላለመካተት እንደ ምክንያት ካነሷቸው ጉዳዮች መካከል የአካል ጉዳተኛ እና አረጋውያን ተገልጋዮች ቁጥር አነስተኛ መሆን፣ የበጀት እጥረት እና የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን መብቶች ላይ ግንዛቤ ማስጨበጫ ወይንም ለጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶት እንዲሠሩ ለማድረግ በጋራ የሚሠራ ሌላ ተቋም አለመኖር የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው።

በተጨማሪም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰው ሀብት ልማት ዳይሬክቶሬት በሰጠው መረጃ ለአካል ጉዳተኛ ሠራተኞች የትራንስፖርት ማመቻቸት ሥራ ለመሥራት ታስቦ የነበረ ቢሆንም በጊዜው በጀት ጸድቆ ስላልነበር ወደ ተግባር እንዳልተገባ እና ለቀጣይ በጀት ዓመት ይህን ከግምት በማስገባት እንደሚሠሩ አስረድቷል።

**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የፍትሕ ተቋማት፡** የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ፍትሕ ቢሮ በዚህ ክትትል የተሸፈኑትን የክልሉ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤት እና የክልሉ ሰነዶች፣ ማኅበራት እና ጠበቆች ምዝገባ ጽሕፈት ቤትን ጨምሮ ሌሎች ተጠሪ ጽሕፈት ቤቶችን የያዘ ተቋም ነው። በዚህም መሠረት የክልሉ ሰነዶች፣ ማኅበራት እና ጠበቆች ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ተጨማሪ የማጠናከሪያ ሥራዎች የሚፈልግ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የተሻለ ተቋማዊ ተደራሽነት ያለው መሆኑን ኮሚሽኑ ተገንዝቧል። ለዚህም ጥሩ ማሳያ የሚሆነው ጽሕፈት ቤቱ የሚጠቀምበት የሰነድ ማረጋገጥና ምዝገባ የአሠራር ማኑዋል ነው። የአሠራር ማኑዋሉ ሰነድ የማረጋገጥና የመመዝገብ አገልግሎት ፈልገው ወደ ተቋሙ የሚመጡ ተገልጋዮች የሚስተናገዱበትን ሥርዓት በዝርዝር ያመላከተ ሲሆን፤ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊዎች፣ ባለሙያዎች እና አረጋጋጮች ተግባራዊ እንዲያደረጉት ይጠበቃል።

ይህ የአሠራር ማኑዋል በተለይም መስማት የተሳናቸውና በምልክት ቋንቋ የሚግባቡ ሰዎች ተገልጋይ ሆነው ሲቀርቡ መስማት ከተሳናቸው ማኅበር አስተርጓሚ በደብዳቤ የተመደበላቸው መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚገባ በግልጽ ያስቀምጣል።[7] ይኹንና፤ በአካባቢው የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚዎችን ማግኘት አዳጋች በመሆኑ ይህ ድንጋጌ በተግባር ተፈጻሚ አለመሆኑን ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው የጽሕፈት ቤቱ ባለሙያዎች አስረድተዋል።

የአሠራር ማኑዋሉ ዐይነ ስውራንን ጨምሮ ሌሎች በጣታቸው የሚፈርሙ ሰዎችን በተመለከተ የሰነድ አረጋጋጭ ባለሙያዎች ትኩረት ሰጥተው በመርገጫ ቀለም የጣት ምልክታቸውን በሰነዱ መጨረሻ ላይ እንዲያስቀምጡ እና በጣት ምልክቱ ላይ ስማቸው በሚነበብ መልኩ የተጻፈ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚኖርባቸው በግልጽ ያስቀምጣል።[8] ይህም ዐይነ ስውራንም ሆኑ አረጋውያን የንብረት መብታቸውን ጨምሮ ሌሎችም ከሰነድ ምዝገባ ጋር የተያያዙ መብቶቻቸው እንዲጠበቁላቸው የሚያደርግ አሠራር መሆኑን ኮሚሽኑ ተመልክቷል።

ቅድሚያ አገልግሎት ማግኘትን በተመለከተ በአሠራር ማኑዋሉ ወይም በሌሎች መመሪያዎች ላይ የተቀመጠ ነገር ባይኖርም አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን በተግባር ቅድሚያ እንዲያገኙ እንደሚደረግ የጽሕፈት ቤቱ ባለሙያዎች እንዲሁም ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው ተግልጋዮች አስረድተዋል።

የክልሉ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ቢሮ በበኩሉ ከአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ጋር በተገናኘ በአብዛኛው ነጻ የሕግ ድጋፍ አገልግሎቶችን እንደሚሰጥ ገልጿል። በተለይም በመኪና አደጋ ምክንያት ዘላቂ ጉዳት ያጋጠማቸው በርካታ አካል ጉዳተኞች የፍትሐ ብሔር ጉዳዮቻቸውን ጠበቃ ከፍለው መከራከር የማይችሉ ስለመሆናቸው ከቀበሌ ወይም ማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች የድጋፍ ደብዳቤ በማምጣት የክልሉ ፍትሕ ቢሮ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1163/2011 በደነገገው መሠረት ሙያዊ አገልግሎት የሚያገኙ መሆኑን ለኮሚሽኑ አስረድተዋል። ከመንግሥት ተከላካይ ጠበቆች በተጨማሪ በግል ጠበቆች ዓመታዊ ነጻ አገልግሎት (pro bono service) እንዲሁም በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ነጻ የሕግ ድጋፍ ማእከል አማካይነት ድጋፍ እንዲያገኙ እንደሚደረግ ገልጸዋል።

በአጠቃላይ የክልሉ ፍትሕ ቢሮም ሆነ በሥሩ የሚገኙትና በዚህ ክትትል የተሸፈኑት ተጠሪ ጽሕፈት ቤቶች የአካል ጉዳተኞችን እና የአረጋውያንን ተካታችነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ራሱን የቻለ ፖሊሲ፣ መመሪያ ወይም ደንብ የሌላቸው መሆኑ ነገር ግን አካል ጉዳተኞችን እና አረጋውያንን በተመለከተ ውስን የሕግ ድንጋጌዎች እና የአሠራር ማኑዋሎች መኖራቸው በክትትሉ ተለይቷል። በተጨማሪም በዓመታዊ ዕቅዶቻቸው ውስጥ የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን ተካታችነትና ምቹ አገልግሎት ለማረጋገጥ የሚያስችል የዕቅድ ክንውን እና የፋይናንስ ዕቅድ አለመኖሩ፣ ሴቶችና ሕፃናት አካል ጉዳተኞችን እንዲሁም የአእምሮ እድገት ውስንነት እና የማኅበረ ሥነ-ልቦና ጉዳተኞችን ማእከል ያደረገ የአሠራር ሥርዓት አለመኖሩ እንዲሁም አካል ጉዳተኛ ሠራተኞች አለመኖራቸውም በተደረገው ክትትል ለማወቅ ተችሏል።

የባምባሲ ወረዳ ፍትሕ ጽሕፈት ቤት የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን ተካታችነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ራሱን የቻለ ፖሊሲ፣ መመሪያ ወይም ደንብ እንዲሁም ዝርዝር ተግባራትን የያዘ ዓመታዊ ዕቅድ የሌለው ቢሆንም በ2015 በጀት ዓመቱ የተለዩ የትኩረት አቅጣጫዎችን ለማሳካት

---

[7] የሰነድ ማረጋገጥና መመዝገብ የአሠራር ማንዋል፣ ገጽ 26 እና ገጽ 29

[8] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 29

የሚኖሩ ተግባራት በሚለው ሥር ‹‹ትኩረት በሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚፈጸሙ የመብት ጥሰቶችን ተከታትሎ ማስተካከል … አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን በመብታቸው እኩል ተጠቃሚነታቸውን ማስከበር›› የሚል የስኬት አመላካች የተቀመጠ መሆኑ በተደረገው ክትትል ለማወቅ ተችሏል። ይኹንና አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን እንደ ሴቶችና ሕፃናት ሁሉ የተጋላጭነት ሁኔታቸው ከፍ ያለ በመሆኑ እና የትኩረት አቅጣጫዎቹን ለማሳካት አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት እንደ አንድ የስኬት አመላካችነት የተቀመጠ በመሆኑ፤ ዓመታዊ ዕቅዱ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን የተመለከቱ ዝርዝር ተግባራት ሊያካትት ይገባል።

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልሉ ሕገ መንግሥት እና በክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ 163/2011 መሠረት የተቋቋመ የዳኝነት አካል ሲሆን፤ የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን ተካታችነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ራሱን የቻለ ፖሊሲ፣ መመሪያ ወይም ደንብ የሌለው መሆኑ በክትትሉ ተለይቷል። ጠበቃ የማቆም መብት በማቋቋሚያ አዋጁ አንቀጽ 24 ሥር ዕውቅና የተሰጠው ሲሆን፤ ጠበቃ ማቆም የማይችል ተከሣሽ በመንግሥት ተከላካይ ጠበቃ ሊመደብለት እንደሚችል ያስቀምጣል። በተግባርም አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን ጨምሮ ማንኛውም ግለሰብ ይህንን መብት እንዲያገኝ እንደሚደረግ የፍርድ ቤቱ ኃላፊዎች ለኮሚሽኑ ገልጸዋል።

በተጨማሪም አካል ጉዳተኛ እና አረጋውያን ባለጉዳዮች በሬጅስትራር ቢሮዎችና በችሎቶች ውስጥ ቅድሚያ አገልግሎት እንዲያገኙ እንደሚደረግ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ዳኞች እና የሬጅስትራር ባለሙያ ለኮሚሽኑ ገልጸዋል። ይህ አሠራርም የተቋሙ የሥራ አመራር ሂደት በተመለከተ በተደረገው የቢፒአር (Business Process Reengineering - BPR) ጥናት ውስጥ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተገልጋዮች ትኩረት እንደሚሰጣቸው እና በአግልግሎት ወቅትም ቅድሚያ እንዲሰጣቸው የሚገልጽ መሆኑን ኃላፊዎቹ ተናግረዋል። ይኹንና የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ዳኞችም ሆኑ ሌሎች ባለሙያዎች በአገልገሎት ወቅት ቅድሚያ የሚሰጡት በራሳቸው ተነሳሽነት በመሆኑ፤ የፍርድ ቤቱን ተቋማዊ ተደራሽነት ለማጠናከር እንዲረዳ ይህን ሰነድ ማስተዋወቅ እና አፈጻጸሙን በየጊዜው ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል።

በተጨማሪም በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ያለ አንድ የማኅበራዊ ሳይንስ ባለሙያ የአእምሮ ሕመም ያለባቸው ባለጉዳዮችን ለማስተናገድ ድጋፍ እንደሚያደርግ ለኮሚሽኑ ገልጸዋል። በሌላ በኩል የአእምሮ ሕመም እንዳለባቸው ግምት የተወሰደባቸው የወንጀል ድርጊት ተጠርጣሪዎችን ያሉበትን የጤና ሁኔታ ለማወቅ ወደ አዲስ አበባ እንደሚላኩ እና በሕክምና ውጤቱ መሠረት የፍርድ ሂደቱ እንዲቀጥል እንደሚደረግ አስረድተዋል።

በክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለሕፃናት ምቹ የሆነ ችሎት (child friendly bench) በአጋር አካላት ድጋፍ ያቋቋመ ሲሆን፤ በክትትሉ ወቅት ካሜራዎቹ አገልግሎት መስጠት በማቆማቸው አገልግሎት እየሰጠ እንዳልሆነ ለማወቅ ተችሏል። ሴት አካል ጉዳተኛና አረጋውያን ባለጉዳዮችን በተመለከተ በተለይም ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት ተጎጂዎች ጉዳዮችን በዝግ ችሎት እንዲታዩ የሚያደርጉበት አሠራር መኖሩን የፍርድ ቤቱ ኃላፊዎች ለኮሚሽኑ ገልጸዋል።

በአሶሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ባለጉዳዮች ቅድሚያ አገልግሎት እንዲሰጥ የሚያስገድድ መመሪያ ባይኖርም በአገልግሎት ወቅት ቅድሚያ እንዲያገኙ እንደሚደረግ፣ ነጻ የሕግ ድጋፍ ለሚፈልጉ ባለጉዳዮችም በመንግሥት ተካላካይ ጠበቃና በአሶሳ

ዩኒቨርሲቲ ነጻ የሕግ ድጋፍ ማእከል አማካይነት እንዲያገኙ እንደሚደረግ፣ በፍርድ ቤቱ የሥነ-ልቦና ባለሙያ አማካይነት የባለሙያ እገዛ በሚሹ ጉዳዮች ላይ ድጋፍ እንደሚያገኙ እንዲሁም ለሕጻናት ምቹ የሆነ ችሎት በማደራጀት አስፈላጊ የሆኑ መገልገያዎችን በማሟላት አገልግሎት ማስጀመራቸውን የፍርድ ቤቱ ኃላፊዎች ለኮሚሽኑ አስረድተዋል፡፡

የባምባሲ ወረዳ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ተካታችነትን በተመለከተ አገልግሎት ቅድሚያ እንዲያገኙ እንደሚደርግ፣ በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ነጻ የሕግ ድጋፍ ማእከል አማካይነት ነጻ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ እንደሚደረግ፣ እንደ ጉዳዩ ክብደት የሚመዘን ሆኖ አካል ጉዳተኛ እና አረጋውያን ባለጉዳዮች በፍጥነት እልባት እንዲያገኙ የሚያስችል አሠራር ያለው መሆኑ፣ የማኅበረ-ሥነ ልቦና ድጋፍ ለሚሹ ባለጉዳዮች በማኅበራዊ ሳይንስ ባለሙያ በኩል እገዛ የሚደረግላቸው መሆኑ ኮሚሽኑ በክትትሉ ለማወቅ ችሏል፡፡

በተጨማሪም የባምባሲ ወረዳ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመንግሥት ተከላካይ ጠበቃን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ ለዚህ ዓላማ ተብሎ የተቀጠረ ባለሙያ አለመኖሩን ኮሚሽኑ ተረድቷል፡፡ በፍርድ ቤቱ ለሕፃናት ምቹ የሆነ ችሎት በአጋር አካላት ድጋፍ ተቋቁሞ የነበረ ቢሆንም በክትትሉ ወቅት ካሜራዎቹ አገልግሎት መስጠት በማቆማቸው ዳኞች ሕፃናትን የተመለከቱ ጉዳዮችን በሙሉ በተለመደው ችሎት እንዲያስችሉ መገደዳቸው ኮሚሽኑ አሳሳቢ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

*በአዲስ አበባ ከተማ የፌዴራል ፍትሕ ተቋማት ፡* ክትትል የተካሄደባቸው የፍትሕ ተቋማት አካል ጉዳተኞችን እና አረጋውያንን ማካተትን በተመለከተ የጽሑፍ ፖሊሲም ሆነ የበጀት ዕቅድ የላቸውም፡፡ ነገር ግን በክትትሉ ላይ በተዳሰሱት ፍርድ ቤቶች አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ተገልጋዮች በሚመጡ ጊዜ ቅድሚያ እንዲገለገሉ የሚያስችል የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያ ያለ መሆኑን እና ይህም በፍርድ ቤት ዕቅድ ውስጥ እንደሚካተት እና አተገባበሩን ለማወቅም በየክፍሎቹ ቁጥጥር እንደሚደረግ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

በዚህ መመሪያ መሠረት አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ለመስተናገድ በሚመጡበት ወቅት ቅድሚያ እንዲስተናገዱ የሚያደርግ ቅድሚያ የሚል ባጅ እና ፎርም እንዳለ በዚያም መሠረት ቅድሚያ እንደሚስተናገዱ የፍርድ ቤት ሬጅስትራር ሠራተኞች ለኮሚሽኑ ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ አሠራር የፍትሕ ቢሮ ጽሕፈት ቤቶች መሰል መመሪያ ባይኖራቸውም አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ቅድሚያ አገልግሎት እንዲያገኙ የሚደረግበት ሁኔታ መኖሩን ኮሚሽኑ በክትትሉ ወቅት ያገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ 943/2008 በአንቀጽ 6(4) (ሠ) ላይ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍትሐ ብሔር ክስ ለመመሥረት የገንዘብ ዐቅም የሌላቸውን ዜጎች በተለይም ሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ አካል ጉዳተኞችን እና አረጋውያንን ወክሎ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ እንደሚከራከር ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሠረት አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን በፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ላይ በዐቃቤ ሕግ የሚወከሉ እና ጉዳያቸው እንዲታይ እንደሚደረግ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በተጨማሪም የፍትሕ ሚኒስቴር የሴቶች፥ ሕፃናት እና ባለብዙ ዘርፍ ዳይሬክቶሬት ያለው ሲሆን፤ ይህ ዳይሬክቶሬት ከሴቶች እና ሕፃናት በተጨማሪ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ኤች.አይ.ቪ በደማቸው የሚገኝ ሰዎችን ጉዳይ አቅፎ የያዘ ነው፡፡ ይህ ዳይሬክቶሬት የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሥራ ክፍሎች እንዲሁም ተጠሪ ተቋማት የሴቶች፣ ሕፃናትና ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን አስመልክቶ በምን መልኩ አካትተው መሥራት እንደሚገባቸው፣ የተሠሩ ሥራዎችን

በምን መልኩ ሪፖርት ማድረግ እንደሚገባቸው የሚያትት እንዲሁም በአጠቃላይ በተቋሙ እነዚህን ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ያማከሉ የተሠሩ ሥራዎች ለማወቅ፣ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል ማካተቻ መምሪያ (guideline) ያዘጋጀ ሲሆን ይህም የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን የፍትሕ ተደራሽነት መብትን ለማረጋገጥ እንደሚረዳ የተቋሙ ባለሙያዎች ለኮሚሽኑ ገልጸዋል።

ፍትሕ ሚኒስቴር በርካታ ቁጥር ያላቸው አካል ጉዳተኛ ሠራተኞች ያሉት ሲሆን እነዚህ ሠራተኞች ባቀረቡት ቅሬታ መሠረት ተቋሙ የዳሰሳ ጥናት አካሂዷል። የዳሰሳ ጥናቱ የተቋሙ አካል ጉዳተኛ ሠራተኞች እየገጠሟቸው ያሉትን ተግዳሮቶች የሚዳስስ ሲሆን በዚህ ጥናት ከተለዩ ተግዳሮቶች መካከል የረዳት አንባቢ አለመኖር፣ ከሥራ ቦታ ምቹነት እና ምደባ ጋር የተገናኙ ተግዳሮቶች፣ የቢሮ መገልገያዎችና የትራንስፖርት ችግር፣ የሥራ ላይ ስልጠናና የትምህርት ዕድል አለመመቻቸት እና የዐቃቢያነ ሕግ የመኖሪያ ቤት ድልድል ችግሮች ተጠቃሽ መሆናቸውን ኮሚሽኑ ተገንዝቧል።

ለእነዚህ ተግዳሮቶች መፍትሔ ይሆናሉ ተብለው ከቀረቡ ምክረ ሐሳቦች መካከል የረዳት አንባቢ ቅጥር ሲፈጸም የዐይነ ስውራንን ተሳትፎ ማረጋገጥ፤ በተቋሙ የአካል ጉዳተኞች ማስተባበሪያ ክፍል እንዲኖር ማድረግ፣ የአካል ጉዳተኛ ሠራተኞች ጉዳይን በዕቅድና በበጀት ውስጥ በማካተት ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኝ ማድረግ፣ ለአካል ጉዳተኛ ሠራተኞች ለሥራ አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶች በወቅቱና በተገቢው ጊዜ እንዲሟሉ ማድረግ፤ ለበላይ አመራሮች እና ለሠራተኞች አካል ጉዳተኞችን አስመልክቶ የግንዛቤ ስልጠና መስጠት፤ የተለየ ስልጠናና የትምህርት ዕድል ለአካል ጉዳተኞች መስጠት፤ መጽሐፍት በድምፅ ወይም በሶፍትኮፒ እንዲዘጋጁ ማድረግ፤ የሥራ ቦታን ለአካል ጉዳተኞች ምቹ እንዲሆን ማድረግ የሚሉት ይገኙበታል።

## ከባቢያዊ ተደራሽነት

***የአፋር፣ አማራ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ኦሮሚያ፣ ሶማሊ እና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ፍትሕ ተቋማት*** ሕንጻዎች መግቢያ ደረጃ ብቻ ያላቸው እና ራምፕ ያልተገነባላቸው ሲሆኑ የችሎት አዳራሾች እና መጸዳጃ ቤቶች ለአካል ጉዳተኞች በተለይም ለተሽከርካሪ ወንበር ተጠቃሚዎች ተደራሽ ያልሆኑ መሆኑን ኮሚሽኑ ተመልክቷል። ለአብነት የአፋር ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሕንጻ ከአንድ በላይ ወለል ያለው ሲሆን፤ የችሎት አዳራሽ እና መዝገብ ቤት ምድር ቤት እንዲሆኑ የተደረገ ቢሆንም ወደ እነዚህ ቦታዎች የሚወስዱ መንገዶች ደረጃ ያላቸውና ራምፕ ያልተገነባላቸው በመሆኑ ተደራሽ አይደሉም። በተጨማሪም በአማራ ክልል በጎንደር ከተማ አስተዳደር ወረዳ ፍርድ ቤት ወደ ኃላፊ ቢሮ እና ሁለት የችሎት አዳራሾች የሚወስደው መግቢያ ላይ ራምፕ ቢኖርም በአጠቃላይ ሲታይ ለአካል ጉዳተኞች የተሟላ ከባቢያዊ ተደራሽነት እንደሌለው እንዲሁም በተመሳሳይ በማእከላዊ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ፍትሕ መምሪያ ወደ ሠነዶችና ማረጋገጫ እና መረጃ ክፍል የሚወስደው መንገድ እንዲሁም ለችሎት የሚመጡ ባለጉዳዮች መጠበቂያና ወደ ችሎት መግቢያ የሚወስደው ራምፕ የተቆፈሩ ቦታዎች ስላሉት ለተሽከርካሪ ወንበር ተጠቃሚዎች ምቹ አለመሆኑን ኮሚሽኑ በአካል ምልከታ ተረድቷል።

በሌላ በኩል በኦሮሚያ ክልል የጅማ ከተማ ፍትሕ ጽሕፈት ቤት በ2014 በጀት ዓመት በኢሰመኮ ጅማ ጽሕፈት ቤት የአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ሰብአዊ መብቶች ላይ በተሰጠው የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ የተቋሙ አመራር በመሳተፍቸው ባገኙት ግንዛቤ የተቋማቸው መግቢያ በር

ላይ ራምፕ እንዲሠራ ማድረጋቸውን ኮሚሽኑ ባደረገው የአካል ምልከታ ተረድቷል፡፡ ሆኖም ኮሚሽኑ በክትትል ሥራው የሸፈናቸው ሌሎች የክልሉ ፍትሕ ተቋማት በተለይ ከእንቅስቃሴ ጋር የተገናኘ አካል ጉዳት ላለባቸው ተገልጋዮች ከባቢያዊ ተደራሽነት የሌላቸው መሆኑን ተረድቷል፡፡

በአጠቃላይ ከባቢያዊ ተደራሽነትን በተመለከተ እነዚህ ተቋማት መድረስ ከሚገባቸው እጅግ ወደ ኋላ የቀሩ መሆናቸውን ኮሚሽኑ ባደረገው ምልከታ ተረድቷል፡፡

**የአዲስ አበባ ከተማ የፌዴራል ፍትሕ ተቋማት** ፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አዲስ ከተማ ምድብ ችሎት ሕንጻው ገና ሙሉ ለሙሉ ያልተጠናቀቀ በመሆኑ አሳንሰር ያልተገጠመለት ሲሆን፤ አሳንሰሩ የሚገጠምበት ቦታ (ሻፍጥ) በከፊል ወለሎች ላይ ምንም ዐይነት መከለያ አልተደረገበትም፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት መግቢያ በር የመኪና መግቢያ ያለው ቢሆንም የተደረገው የአስፓልት ንጣፍ በጣም የተበላሸ ወጣ ገባ የሚበዛበት ነው፡፡ ወደ ሕንጻው ለመግባት ፊት ለፊት የሚታየው ደረጃ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን በሕንጻው መጨረሻ በቀኝ በኩል ራምፕ የሚገኝ ሲሆን፤ ከተጠቃሚ ዕይታ ውጪ በመሆኑ እና አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክት ባለመኖሩ ራምፑን ለመጠቀም አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ወደ ምድብ ችሎቱ የሚወስደው ራምፕ ከፍታ ደረጃውን ያሟላ ቢሆንም በሁለቱም በኩል የእጅ መደገፊያዎች የሉትም፡፡ እንዲሁም የሕንጻው ወለሎች በጣም አንሸራታች በመሆናቸው ለክራንች ተጠቃሚዎች አዳጋች ያደርጋቸዋል፡፡ በተጨማሪም በሕንጻው ግራ ክፍል ያለው በረንዳ ምንም ዐይነት መከለያ (ድጋፍ/አጥር) ያልተሠራለት በመሆኑ ዐይነ ሥውራንን ለአደጋ ሊዳርግ የሚችል ነው፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት የባለጉዳዮች መግቢያ የተሽከርካሪ ወንበር ለሚጠቀሙ እና አካላዊ ጉዳት ላለባቸው አስቸጋሪ እንደሆነ ኮሚሽኑ ተገንዝቧል፡፡ በተመሳሳይ ወደ ሕንጻው መግቢያ ራምፕ የሌለው በመሆኑ የተሽከርካሪ ወንበር ተጠቃሚዎች ወደ ምድብ ችሎቱ ቢሮዎች መግባት አይችሉም፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግቢ የአስፓልት ንጣፍ ያለው መንገድ ቢሆንም መሐል ላይ የተቀመጡት የፍጥነት መቀነሻዎች ትልልቅ በመሆናቸው ለአካል ጉዳተኞች በተለይም ለተሽከርካሪ ወንበር ተጠቃሚዎች አዳጋች ናቸው፡፡ በፍርድ ቤቱ ግቢ ያሉ ሁሉም ባለ ፎቅ ሕንጻዎች አሳንሰር የላቸውም፡፡

በአጠቃላይ ክትትል በተደረገባቸው ፍርድ ቤቶች የችሎት አዳራሾችን በተመለከተ ከአንድ የችሎት አዳራሽ በስተቀር ሌሎቹ አዳራሾች የሚገኙት ፎቅ ላይ በመሆኑ እና አሳንሰር ያልተገጠመ በመሆኑ ተደራሽ አይደሉም፡፡ እንዲሁም ሕንጻዎች ውስጥ የሚገኙት መጸዳጃ ቤቶች ለአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን የተቀመጠውን ዝቅተኛ ደረጃ የማያሟሉና ተደራሽ ያልሆኑ ናቸው፡፡

## የመረጃና ተግባቦት ተደራሽነት

**የአፋር፣ አማራ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ኦሮሚያ፣ ሶማሊ እና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ፍትሕ ተቋማት:** በእነዚህ ክልሎች የሚገኙና ክትትሉ የተካሄደባቸው ፍርድ ቤቶች መዝገብ ሲከፍት፣ ክርክር ሲካሄድ፣ ክስ ሲቀርብ እንዲሁም ምስክር ሲሰማ መስማት ለተሳናቸው ባለጉዳዮች የትርጉም አገልግሎት ባለመኖሩ አብዛኛውን ጊዜ ከቤተሰብ ጋር እንዲቀርቡ

እንደሚደረግ ለመገንዘብ ተችሏል። ሁሉም የፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውኑ በተለይም ነጻ የሕግ ድጋፍ፣ የሰነዶች ማረጋገጫ እና የንቃተ ሕግ ግንዛቤ አገልግሎቶችን በሚሰጡበት ወቅት መስማት ለተሳናቸው መረጃን ተደራሽ ለማድረግ በቤተሰብ እንዲታገዙ እንዲሁም ዐይነ ሥውራንን በተመለከተ ፍርድ ቤቶች እና የፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች በጽሑፍ የሚቀርቡ መረጃዎችን ሌላ ሰው እንዲያነብላቸው በማድረግ መረጃ እንዲያገኙ እንደሚደረግ አስረድተዋል።

በአማራ ክልል ምንም እንኳን አልፎ አልፎ ከትምህርት ተቋማት የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ በማምጣት አገልግሎቱን ለማግኘት ጥረት የሚደረግ መሆኑ ክትትል ከተደረገባቸው ፍርድ ቤቶች ለመረዳት የተቻለ ቢሆንም ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው እና የመስማት ችሎታቸው የቀነሰ አረጋዊ ችሎት ላይ ክስ በሚቀርብበት፣ ክርክሩ በሚደረግበት እና ምስክር በሚሰማበት ወቅት በትክክል ዳኞች የሚሉትን ለመስማት እንደሚቸገሩ፣ ወደ ዳኞች ተጠግተው ለመስማት ሲሞክሩ ራቅ ብለው ይቁሙ ተብለው እንደሚያመናጭቋቸው ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

የአእምሮ ሕሙማንና የአእምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው አካል ጉዳተኞችን ለማስተናገድ ከመረጃና ተግባቦት ተደራሽነት አንጻር በተወካዮቻቸው በኩል ጉዳያቸውን እንዲያስረዱ ለማድረግ ጥረቶች ቢኖሩም አሠራሩ በተለይም በእነዚህ የጉዳት ዐይነቶች ላይ በሰለጠኑ ባለሙያዎች የታገዘ ባለመሆኑ ምቹ አለመሆኑን ክትትል የተደረገባቸው ሁሉም ፍርድ ቤቶች እና የፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች ለኮሚሽኑ ገልጸዋል። ሆኖም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ የአእምሮ ሕመም ወይም የአእምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ሰዎች በመደበኛው የችሎት አቀራረብ ሊፈጠርባቸው በሚችል ድንጋጤ ወይም ፍርኃት እንዲሁም ነገሮችን የሚረዱበት/የሚያዩበት ዘዴ የተለየ በመሆኑ ምክንያት ለመግባባት እንደአስፈላጊነቱ በየፍርድ ቤቶቹ ያሉት የማኅበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች እገዛ የሚያደርጉ መሆኑን ኮሚሽኑ ተገቢ እና ሊጠናከር የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል።

**የአዲስ አበባ ከተማ የፌዴራል ፍትሕ ተቋማት**: ክትትሉ በተደረገባቸው የፍትሕ ተቋማት የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን የመረጃ እና ተግባቦት ፍላጎቶችን ከግምት ያስገቡ የመረጃ እና ተግባቦት አማራጮች የሉም። በተቋማቱ የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ የሌለ እና መስማት የተሳናቸው ባለጉዳዮች አገልግሎት ለማግኘት ኢ-መደበኛ በሆነ መልኩ ራሳቸው የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ ይዘው የሚሄዱ ሲሆን፣ በሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ኤጀንሲ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተመለከተም የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ ባለመኖሩ መስማት የተሳናቸው ተገልጋዮች አገልግሎቱን ለማግኘት የሚቸገሩ መሆኑን ኮሚሽኑ ተገንዝቧል። በክትትሉ በተሸፈኑ ፍርድ ቤቶች የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ በሚያስፈልግበት ወቅት ከአዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ ወይንም መስማት ከተሳናቸው ማኅበር እንደሚያመጡ መስማት የተሳናቸው ተገልጋዮች ለኮሚሽኑ አስረድተዋል፡፡ ተገልጋዮቹ አክለው የፍትሕ ተቋማት ላይ ለመብት ጥሰት እንደሚጋለጡ እና ለዚህም ዋነኛ ምክንያት የመረጃ እና የተግባቦት ክፍተት መሆኑን ገልጸዋል።

ሕፃናትን በተመለከተ ክትትሉ በተደረገባቸው ፍርድ ቤቶች ለሕፃናት የተለየ የችሎት ክፍል ያለ ሲሆን ይህ ክፍል ለሕፃናት አእዕምሮ የሚመጥን እና ከመደበኛ የችሎት አቀራረብ በተለየ ሁኔታ የተዘጋጀ ነው። በወንጀል ጉዳዮች ሕፃናት ከማኅበራዊ ሳይንስ ባለሞያ ጋር በመሆን ቃላቸውን የሚሰጡበት ክፍል ያለ ሲሆን የፍትሐ ብሔር ጉዳይን በተመለከተ ግን ከቤተሰብ ጋር ሆነው ቃል እንደሚሰጡ ኮሚሽኑ ተገንዝቧል። በተመሳሳይ የአእምሮ ሕመም ወይም የአእምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ባለጉዳዮች በወንጀል ጉዳይ ሲመጡ ከተከሳሽ ጋር እንዳይገናኙ እንደሚደረግ

እና ከማኅበራዊ ሳይንስ ባለሞያዎች ጋር በመሆን ቃላቸውን እንዲሰጡ በማድረግ የጥንቃቄ እርምጃ እንደሚወሰድ ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

ነገር ግን በፍትሕ ሚኒስቴር ሥር የሚገኙት በክትትሉ የተካተቱት የዓቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤቶች የአእምሮ እድገት ውስንነት እና የአእምሮ ሕመም ያለባቸው ባለጉዳዮችን የሚያስተናግድ የሥነ ልቦና/ማኅበራዊ ሳይንስ ባለሙያ ከልደታ ዓቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤት በስተቀር እንደሌለ ገልጸዋል። እነዚህን ባለሙያዎች በተቻለ መጠን ለሁሉም ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ተደራሽ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ የፍትሕ ሚኒስቴር የሴቶች፥ ሕጻናት እና ባለብዙ ዘርፍ ዳይሬክቶሬት ለኮሚሽኑ አስረድቷል። ክትትሉ በተደረገባቸው የሚኒስቴሩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ዐቃቤያነ ሕግ የሥነ ልቦና/ማኅበራዊ ሳይንስ ባለሙያ እጥረት እንዳለ አስረድተዋል።

በልደታ ቅርንጫፍ የሴቶች፥ ሕፃናት እና ባለብዙ ዘርፎች ቡድን አስተባባሪ ለኮሚሽኑ እንዳስረዱት የአእምሮ እድገት ውስንነት፣ የአእምሮ ሕመም እንዲሁም ሌሎች ጉዳቶች እና ተደራራቢ ጉዳት ያለባቸው ባለጉዳዮችን ማስተናገድ የሚችል ባለሙያ ወይም በተቋሙ ያሉትን ባለሙያዎች በስልጠና በማጎልበት ለእነዚህ ባለጉዳዮች አግባብ ያለው አገልግሎት እንዲዘረጋ የሚያስችል አሠራር አለመኖሩ የፍትሕ ተደራሽነት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እየፈጠረ እንደሚገኝ ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

ኮሚሽኑ በአጠቃላይ በክትትሉ የተሸፈኑት ፍርድ ቤቶች እና ሌሎች የፍትሕ ተቋማት ያላቸው የመረጃና ተግባቦት ተደራሽነት እጅግ ዝቅተኛ መሆኑን ተረድቷል። በችሎት ላይም ሆነ ከችሎት ውጪ ባለው የፍርድ ቤቶች አገልገሎት ሁሉ ለአካል ጉዳተኞች የጉዳት ዐይነታቸውን ያገናዘበ የመረጃና ተግባቦት ማመቻቸት አይደረግላቸውም። ሁሉም ክትትሉ የተደረገባቸው ፍርድ ቤቶች እና የፍትሕ ተቋማት የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ ባለሙያ የሌላቸው መሆኑ እና ለዐይነ ስውራን ክስ በብሬይል፣ በሶፍት ኮፒ ወይም በድምፅ ቅጂ እንዲደርሳቸው ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት የሌላቸው መሆኑ በክትትሉ ከተለዩ የመረጃና ተግባቦት ተደራሽነት ክፍተቶች መካከል ተጠቃሽ ናቸው።

## የአመለካከት መሰናክሎች

በሁሉም ክትትል በተደረገባቸው የፍትሕ ተቋማት የሚሠሩ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ሰነድ ተቀርጾ በተደራጀ መንገድ ስለአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ሰብአዊ መብቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንዳላገኙ ለኮሚሽኑ አስረድተዋል። በተጨማሪም ኮሚሽኑ ቃለ መጠይቅ ያደረገላቸው አንዳንድ የፍትሕ ተቋማት ሠራተኞች በቃለ መጠይቅ ወቅት አግባብነት የሌላቸው ክብረ ነክ ቃላትን፣ ለምሳሌ አካላዊ ጉዳት ያለባቸውን ሰዎች ለመግለጽ *'አካለ ጎዶሎ'* እያሉ ሲጠሩ ተስተውሏል።

ለአብነትም በአማራ ክልል ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው የፍትሕ ተቋማት ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ ወቅት ተብታባ፣ ዲዳ፣ ዘገምተኛ፣ ጤነኛ፤ መልካም ቁመና ያለው የሚሉ አግባብነት የሌላቸውን ቃላት ሲጠቀሙ እንዲሁም፣ አካል ጉዳተኞች ማኅበራዊ ተግባቦታቸው ዝቅተኛ ነው ብሎ በማሰብ አካል ጉዳተኞችን ነጭናጫ በማለት ሲገልጹ ተስተውሏል።

*"[ማየትና መስማት የተሳናቸው ሰዎች ወደ ፍርድ ቤታችን እንዳይመጡ ዱዓ እናደርጋለን እንዴት ልናስተናግዳቸው ነው ከእነርሱ ጋር ማውራት ከባድ ነው]" አንድ የአፋር ፍርድ ቤት ኃላፊ*

*"[ ተብታባ እና ዲዳ]" በማለት አካል ጉዳተኞችን ገልጸዋል። (አንዳንድ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የፍትሕ ተቋማት ሠራተኞች)*

*"[አካል ጉዳተኞች ምን ሊያደርጉ ይሄዳሉ፣ የሰነዶች ሥራ የሀብታሞች ጉዳይ ነው]" (አንድ የአማራ ክልል ፍትሕ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ)*

*"[አካል ጉዳተኞች] ለምስክርነት በቂ አይደሉም" (አንድ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ዐቃቤ ሕግ በተለይም መስማት ከተሳናቸው ሰዎች አንጻር የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ ባለመኖሩ እና ከእንደዚህ ዐይነት ሰዎች ጋር ተግባብቶ የምስክርነት ቃላቸውን መቀበል አይቻልም በሚል እምነት ከተናገሩት)*

*"[እጁ የሰለለ]" በአዲስ አበባ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው አንዳንድ የፍርድ ቤት ሠራተኞች የአካል ጉዳት ዐይነትን ሲገልጹ የተጠቀሙት ቃል*

ኢሰመኮ ያነጋገራቸው አብዛኛዎቹ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን መብቶቻቸውን ከማወቅ እና እንዲከበርላቸው ከመጠየቅ አንጻር የግንዛቤ ክፍተቶች ያለባቸው በመሆኑ መብትን መሠረት ያደረገ ጥያቄ እንደማያቀርቡ እና ጉዳዮች የሚፈጸሙላቸው በፍትሕ ተቋማቱ ቅንነትና ችሮታ ነው የሚል አመለካከት ያላቸው መሆኑን ኮሚሽኑ ተገንዝቧል። ከአማራ ክልል በተገኘው መረጃ መሠረትም አልፎ አልፎ በአካል ጉዳታቸው ምክንያት ያልተገባ ፍርድ እንዲሰጥላቸው የሚፈልጉ፣ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው የሚያስቡ እና ወደ ፍትሕ ተቋማት በመሄድ መብትን ለማስከበር የማይደፍሩ አካል ጉዳተኞች መኖራቸውን ኮሚሽኑ ያገኘው መረጃ ያሳያል።

የኦሮሚያ እና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ማኅበራት ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ቀናትን ከሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ጽሕፈት ቤቶች ጋር በመተባበር ከማክበር የዘለለ ትርጉም ያለው ተሳትፎና የፍትሕ ሥርዓት ሁለንተናዊ ተደራሽነት እንዲኖረው ለማድረግ ከፍትሕ ተቋማት ጋር የሥራ ግንኙነት በመፍጠር የሠሩት ሥራ አለመኖሩን ገልጸዋል።

*"[የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን መብቶች ጉዳይ በፍርድ ቤቶች ዕቅድ ውስጥ የማይካተተው አካል ጉዳተኛ እና አረጋውያን ተገልጋዮች ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ ነው]" (ክትትል የተደረገባቸው አንዳንድ የፍርድ ቤቶች ኃላፊዎች)*

የፍትሕ ሚኒስቴር እንደ ተቋም ንቃተ ሕግ የመስጠት ኃላፊነት ያለበት ቢሆንም በሰው ኃይል እጥረት ምክንያት ስልጠና እየተሰጠ እንዳልሆነ እና ስለ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ሰብአዊ መብቶች በተለይም የፍትሕ ተደራሽነት ላይ በስልጠና የጎለበተ ዕውቀት እንደሌላቸው በክትትሉ ወቅት ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው በአዲስ አበባ የሚገኙ ሠራተኞች ገልጸዋል።

በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሴቶች፣ ሕፃናት እና ባለብዙ ዘርፍ ዳይሬክቶሬት የአካል ጉዳተኞች ቀንን አስመልክቶ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ለተወሰኑ የተቋሙ ሠራተኞች የተሰጠ ቢሆንም ከዚህ በዘለለ የተሠሩ ሥራዎች እንደሌሉም አስረድተዋል። በተጨማሪም የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች የሥነ ልቦና ጉዳት ያለባቸው ባለጉዳዮች አገልግሎት ፈልገው ሲሄዱ ባለሙያ ባይኖራቸውም በመልካም ፈቃዳቸው የሚያስተናግዷቸው መሆኑን ገልጸዋል።

*"[የሥነ ልቦና/ማኅበራዊ ሳይንስ ባለሙያ እጥረት ስላለ እንደዚህ ዐይነት ጉዳዮችን በራሳችን ጥረት እና በጎ ፍቃድ እናስተናግዳለን]" አንዳንድ የፍትሕ ሚኒስቴር ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ዐቃቤያነ ሕግ*

# ክፍል አራት

## ማጠቃለያ እና ምክረ ሐሳቦች

የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ፍትሕ የማግኘት መብት ኢትዮጵያ ፈርማ የሀገሪቱ የሕግ አካል ባደረገቻቸው የዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣ አህጉራዊ እንዲሁም ብሔራዊ የሕግ ማዕቀፎች እና መርሖዎች ዕውቅና የተሰጠው ነው።

አካል ጉዳተኞችን እና አረጋውያንን ጨምሮ የማንኛውንም ሰው ሰብአዊ መብቶችን የማክበር፣ የማስከበር እና የማስፋፋት ቀዳሚ ግዴታ የመንግሥት መሆኑ ይታወቃል። በተለይም የአካል ጉዳተኞችና የአረጋውያን መብቶች እንዲከበሩ እንዲሁም የመብቶች ጥሰት ውጤታማ በሆነ መልኩ ምላሽ እንዲያገኝ የፍትሕ ተቋማት አገልግሎቶች መሟላታቸውን እና ተደራሽ መሆናቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት። በመሆኑም የፍትሕ ተቋማትን ሁለንተናዊ ተደራሽነት ለማረጋገጥ የሚደረጉ ጥረቶች የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያንን ሰብአዊ መብቶች የማክበር፣ የማስከበር እና የማሟላት ግዴታን ለመወጣት እንደሚከናወን ኃላፊነት እንጂ እንደ ችሮታ ሊታይ አይገባውም። በአጠቃላይ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን በፍትሕ ተቋማት የሚያጋጥማቸውን የተቋማዊ፣ ከባቢያዊ፣ የመረጃና ተግባቦት እንዲሁም የአመለካከት መሰናክሎችን በማስወገድ የፍትሕ ተቋማትን ተደራሽነት እና አካታችነት ለማሳደግ የሚረዱ ተግባራዊ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል። ለዚህም አፈጻጸም ይረዳ ዘንድ ኢሰመኮ ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ዝርዝር ምክረ ሐሳቦች ያቀርባል።

## ምክረ ሐሳቦች

- ክትትሉ የተከናወነባቸው እና በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች እና ፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን የሚገጥማቸውን ተቋማዊ መሰናክሎች በማስወገድ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ የሚረዱ አዳዲስ ሕጎችን፣ ፖሊሲዎችን እንዲሁም የአሠራር ሥርዓቶችን እንዲያወጡ እና ክፍተት በታየባቸው ነባር ሕጎች፣ ፖሊሲዎች እና የአሠራር ሥርዓቶች ላይ ተገቢውን ማሻሻያዎች እንዲያደርጉ፤
- ክትትሉ የተከናወነባቸው እና በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች እና ፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን የሚገጥማቸውን ከባቢያዊ ተግዳሮቶች ለማስወገድ በሁሉም መግቢያ በሮች ራምፕ እንዲያስገነቡ፣ በፎቆች ላይ አሳንሰር እንዲያስገጥሙ፣ በምድረ ግቢያቸው ውስጥ ለእንቅስቃሴ እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን እንዲያጸዱ እና ግንባታ ለሚያስፈልጋቸው የማስተካከያ ግንባታ እንዲያደርጉ እንዲሁም የመጸዳጃ ቤቶቻቸውን ተደራሽ ለማድረግ ማሻሻያ ግንባታዎችን እንዲያካሂዱ፤
- ክትትሉ የተከናወነባቸው እና በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች እና ፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ከመረጃ እና ተግባቦት ጋር በተገናኘ የሚገጥማቸውን ተግዳሮት ለማስወገድ በቋሚነት የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ እንዲቀጥሩ፣ በጊዜያዊነት መስማት ከተሳናቸው ማኅበራት ጋር በቅርበት በመሥራት የትርጉም አገልግሎት ማግኘት የሚችሉበትን ሁኔታ እንዲያመቻቹ፣ በመንቀሳቀሻ ቦታዎች ግልጽ የሆኑ ጠቋሚ ምልክቶችን እንዲያስቀምጡ እንዲሁም ለዐይነ ስውራን ክስ፣ መልስ

እና ማናቸውም በቀለም ጽሑፍ የተዘጋጁ የሚመለከቷቸውን ሰነዶች በድምፅ ቅጂ ወይም በብሬል እንዲደርሳቸው በማድረግ ተደራሽነታቸውን እንዲያረጋግጡ፤

- ክትትሉ የተከናወነባቸው እና በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች እና ፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ከአመለካከት ጋር በተገናኘ የሚገጥማቸውን ተግዳሮት ለማስወገድ አመራር እና ሠራተኞችን ጨምሮ ለዳኞች እና ለዓቃብያነ ሕግ የስልጠና ፍላጎትን መሠረት ያደረገ የሰብአዊ መብቶች ስልጠና እንዲሰጣቸው እንዲያደርጉ፤ እንዲሁም ከአመለካከት ጋር በተገናኘ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ላይ የሚደርሱ ጫናዎችን ለመቀነስ ቅሬታ የሚያቀርቡበትን እና አፋጣኝ ምላሽ የሚያገኙበትን ሁኔታ እንዲያመቻቹ፤
- የፍትሕ ሚኒስቴር እና ክትትሉ የተካሄደባቸው ክልሎች የፍትሕ ቢሮዎች በሥራቸው የሚገኙ የፍትሕ ተቋማትን ተቋማዊ፣ ከባቢያዊ፣ የመረጃና ተግባቦት እንዲሁም የአመለካከት ሁኔታ ለማሻሻል የሚያስችል ድጋፍ እና ክትትል እንዲያደርጉ ፤
- ክትትሉ የተከናወነባቸው እና በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች እና ፍትሕ ጽሕፈት ቤቶች የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን ተካታችነት ለማረጋገጥ የሚያስችል በቂ በጀት መያዙን እንዲያረጋግጡ፤
- የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ የክልል ምክር ቤቶች፣ ገንዘብ ሚኒስቴር እና በየክልሉ የሚገኙ የገንዘብ ቢሮዎች የፍትሕ ተቋማት የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን ተካታችነት ለማረጋገጥ የሚያስችል በቂ በጀት የተመደበላቸው መሆኑን እንዲያረጋግጡ፤
- የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በሁሉም ፍርድ ቤቶች እና የፍትሕ ተቋማት የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ መኖሩን ለማረጋገጥ የሥራ መደቡ እንዲኖር እንዲያደርግ፤
- በዚህ የሰብአዊ መብቶች የክትትል ሥራ ያልተሸፈኑ ነገር ግን መሰል ተቋማዊ፣ ከባቢያዊ፣ የመረጃና ተግባቦት እንዲሁም የአመለካከት ተግዳሮቶች የሚስተዋሉባቸው ሁሉም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች እና የፍትሕ ተቋማት በዚህ ሪፖርት የተሰጡ ምክረ ሐሳቦችን እንዲፈጽሙ።